# ወንጌላት

ትምህርት
አምስት

## የዮሐንስ ወንጌል

ተርጓሚ፡ እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM
MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጉሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሌ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ጎብኙ፡፡

**ማውጫ**


1. **መግቢያ**
2. **ዳራ**
   ሀ. ጸሐፊ
      1. ትውፊታዊ አመለካከት
      2. ግለ ታሪክ
   ለ. ወቅት
      1. ቦታ
      2. ተደራሲያን
      3. ቀን
      4. ዓላማ
3. **ውቅርና ይዘት**
   ሀ. መግቢያ
   ለ. የኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት
      1. ለአገልግሎት መዘጋጀት
      2. የመጀመሪያው ፋሲካ
      3. ስም ያልተሰጠው በዓል
      4. ሁለተኛው ፋሲካ
      5. የዳስ በዓል
      6. የቤተ መቅደስ መታደስ በዓል
      7. ሦስተኛው ፋሲካ
   ሐ. ኢየሱስ ላመኑበት የሰጠው አገልግሎት
      1. የመጨረሻው እራት
      2. ሞትና ትንሣኤ
   መ. ማጠቃለያ
4. **ዐቢይ መሪ ሃሳቦች**
   ሀ. ማመን
   ለ. ክርስቶስ
      1. መቅደስ
      2. በዓላት
      3. ህግ
   ሐ. የእግዚአብሔር ልጅ
      1. መለኮት
      2. ሰው
   መ. ሕይወት
5. **ማጠቃለያ**

# 1. መግቢያ

ስሟ ሶፊያ ነው፡፡ ግን እውነተኛ ስሟ አይደለም፡፡ በኢየሱስ ከማመኗ የተነሳ ሊገድሏት ከሚፈልጉ ቤተሰቦቿና ከጓደኞቿ ለመሰወር የምትጠቀምበት ስም ነው፡፡ ሶፊያ የመጣችው በኢየሱስ ማመን ስደት ከሚያስከትልበት ዳራ ነው፡፡ ይህ ነገር ዛሬ በብዙ የዓለም ክፍሎች ውስጥ እውነት ነው፣ በመጀመሪያውም ክፍለ ዘመን እውነት ነበር፡፡ በሐዋርያው ዮሐንስም ዘመን፣ አይሁድ አማኞች ኢየሱስ ለጥንት አባቶቻቸው የተነገሩ ተስፋዎች ፍፃሜ መሆኑን በማመናቸው ምክንያት ከምኩራቦች ይባረሩ ነበር፡፡ ከቤተሰብ ግንዳቸው፣ ከታሪካቸውና ከሃይማኖታቸው ይወገዳሉ፡፡ ዮሐንስም የጻፈው ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ለነዚያ በስደት ላይ ላሉ አማኞች ሊያረጋግጥላቸው ነበር፡፡ እጅግ ፈታኝ በሆነው ሁኔታቸው ውስጥም እንኳን ለኢየሱስ ታማኝ ሆነው ሊዘልቁና በእርሱ የተትረፈረፈ ሕይወትንም ሊያገኙ እንደሚገባቸው ሊያስረግጥላቸው ፈልጓል፡፡

ወንጌላት በተሰኘው ተከታታይ ትምህርታችህ ይህ አምስተኛው ትምህርት ነው፡፡ በዚህ ተከታታይ ትምህርት፣ ኢየሱስ እንዴት የእግዚአብሔርን መንግሥትና ክብር ወደ ምድር ታሪክ ውስጥ እንዳመጣ የሚዘግቡ አራት መጻሕፍትን ተመልክተናል፡፡ ይህ ትምህርት "የዮሐንስ ወንጌል" የሚል ርእስ አለው፡፡ በዚህ ትምህርት፣ የዮሐንስን ወንጌል በበለጠ ግንዘቤ ልናነብበው፣ በበለጠ ጥልቀት እግዚአብሔርን ልንወድድ እና በክርስቶስ ያገኘነውን ሕይወት በሙላት ደስ ልንሰኝበት በሚያስችለን መንገድ እናጠናዋለን፡፡

የዮሐንስን ወንጌል በሦስት ጠቃሚ መንገዶች እናጠናዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የዮሐንስን ወንጌል ዳራ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ ውቅሩንና ይዘቱን እንመረምራለን፡፡ ሦስተኛ፣ ዐቢይ ርዕሶቹን እንመለከታለን፡፡ የዮሐንሰን ወንጌል ዳራ በማጥናት እንጀምር፡፡

# 2. ዳራ

የዮሐንስን ወንጌል ዳራ ጸሐፊውንና የተጻፈበትን ወቅት በመመልከት እንዳስሰዋለን፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ጸሐፊ ማንነት እንጀምር፡፡

## ጸሐፊ

በቤተክርስቲያን ታሪክ፣ ክርስቲያኖች በዘላቂነት የዚህን ወንጌል ፀሐፊነት ለኢየሱስ ደቀመዝሙር፣ ለያዕቆብ ወንድም እና ለዘብዴዎስ ልጅ ለዮሐንስ ይሰጣሉ፡፡ ዮሐንስ ከኢየሱስ የቅርብ ባልንጀሮች ክልል ውስጥ ከሚገኙት አንዱ ሲሆን፣ በቀደምት ክርስቲያናዊ ማኅበረሰብ ውስጥ ወሳኝ ሚና ነበረው፡፡ የእርሱ አዲስ ኪዳናዊ ጽሑፍ አራተኛው ወንጌል ብቻ ሳይሆን፣ 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ መልዕክቶችንና የዮሐንስን ራዕይንም ያካትታል፡፡

የዮሐንስ ወንጌል ጸሐፊነት በሁለት ደረጃዎች እናጠናለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ሐዋርያው ዮሐንስ ይህን ወንጌል ጽፎታል የሚለው ነገር ተአማኒ ነው የሚለውን ትውፊታዊ አመለካከት እንመለከታለን፡፡

ሁለተኛ ደግሞ፣ የዮሐንስን ግለ ታሪክ እንመረምራለን፡፡ ሐዋርያው ዮሐንስ የአራተኛው ወንጌል ጸሐፊ ነው የሚለውን ትውፊታዊ አመለካከት በመመልከት እንጀምር፡፡

## ትውፊታዊ አመለካከት

> **የዮሐንስ ወንጌል እከሌ ጻፈው የሚል ነገር በቀጥታ ከማይኝባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ መጻህፍት አንዱ ነው፡፡ መጽሐፉን ማን ጻፈው ለሚለው ነገር ቁርጥ ያለ ዐረፍተ ነገር እስከ ሌለ ድረስ፣ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አማኝ ክርስቲያን፣ ይህንን እውቅና መስጠትና እኔ እንደማስበውም ከዚያው መጀመር ይገባናል እላለሁ፡፡ በሁለተኛው ምዕተ ዓመት ግን ተርቱሊያን፣ ኢራኒየስ እና ሌሎች ቁርጥ አድርገው ለሐዋርያው ዮሐንስ ሰጡት፡፡ ስለዚህ ምን አሳመናቸው የሚለውን ጥያቄ መጠየቅ ይገባል፡፡ ምላሹም፣ ምናልባት በሕይወት የቆዩትን ሐዋርያት አግኝተዋቸው ወይም ልክ እንደ እነርሱ እርግጠኛ የዐይን ምስክሮቹ ያህል ማስረጃ መስጠት የሚጭችሉ ቀጣይ ትውልዶችን አግኝተው ይሆናል የሚል ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ወደ ወንጌሉ ትመጡና  ውስጣዊ ማስረጃውን ትመለከታላችሁ፡፡ በዚያም ውስጥ መጽሐፉን ማንም ጻፈው ማን የጻፈው ነገር በሚከናወንበት ወቅት የዐይን ምስክር ሆኖ በስፍራው ተገኝቶ የክንውኑ አካል ነበር ማለት ነው፡፡  ለምሳሌ፣ በጌታ እራት ውስጥ፣ ሰውየው በገበታው ላይ ነበር፣ የተወደደው ደቀመዝሙር ከደቀመዛሙርቱ ጋር በገበታው ላይ ነበር፣ ይህ ደግሞ በጣም ብርቱ ማስረጃ ነው፡፡** (ዶ/ር ስቲቭ ሃርፐር)

አራተኛውን ወንጌል ዮሐንስ ጽፎታል የሚለውን እንድንቀበል የምንቀበለው ቢያንስ በሦስት ጥንታዊ ማስረጃዎች ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ የዮሐንስን ወንጌል ጥንታዊ የእጅ ጽሁፎች እናያለን፡፡

## የእጅ ጽሁፎች

የአራተኛው ወንጌል በርካታ ጥንታዊ የእጅ ጽሁፎች የጸሐፊውን ስም ለዮሐንስ ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ፓፒረስ 66 እና ፓፒረስ 75፣ ሁለቱም በ200 ዓ.ም. አካባቢ ተጽፈዋል፣ ወንጌሉን *euangelion kata Iōannēn* በማለት የሚጠሩት ሲሆን፣ ፍቺውም "**የዮሐንስ የጻፈው ወንጌል**" ማለት ነው፡፡ ደግሞም *Codex Sinaiticus* እና *Codex Vaticanus*, ሁለቱም በአራተኛው ምዕተ-ዓመት አጋማሽ የተጻፉ ሲሆን፣ *kata Iōannēn* ብለው ይጠሩታል፣ ፍቺውን "**ዮሐንስ እንደጻፈው**" ማለት ነው፡፡

እርግጥ ነው፣ ዮሐንስ የሚለው ስም የማይታወቅ ስም አልነበረም፡፡ ከቀደሙት የጥንት ጽሑፎች እንደምነረዳው ግን ይህ የጸሐፊነት ሥልጣን ግን ለአንድ ወሳኝ እና በቅዱሳት መጻሕፍት ለተጠቀሰው፣ "**ዮሐንስ**"፣ ለሐዋርያው ዮሐንስ፣ በዓላማ የተሰጠ ነው፡፡

አራተኛውን ወንጌል ዮሐንስ እንደ ጻፈው ጥንታዊ የእጅ ጽሁፎች ማመልከታቸው ብቻ ሳይሆን፣ በወንጌሉ ውስጥ ያሉት ውስጣዊ ማስረጃዎችም ጸሐፊው ዮሐንስ ነው የሚለውን እንድንቀበል ያደርጉናል፡፡

## ውስጣዊ ማስረጃ

የወንጌሉ ጸሐፊ በአንዳንድ የአይሁድ ህግ ነጥቦች ላይ ኢየሱስና የአይሁድ አለቆች ያደርጉ የነበረውን ክርክር ዘግቧል፡፡ እነዚህም ክርክሮች ልክ እንደ ሐዋርያው፣ ዮሐንስ፣ የፓለስታይን አይሁድ እንደሚኖረው አይነት የአይሁድን ህግ ጠንቅቆ የሚያውቅ መሆኑን ያሳያሉ፡፡

ነገሩን ዘለቅ ብለን ስንመለከተው፣ የወንጌሉ ጸሐፊ በእርግጥም የፓለስታይን አይሁድ ለመሆኑ ጠንካራ ማስረጃ አለ፡፡ ይህ የወንጌሉ ፓለስቲንያዊ ባህርይ በኢየሱስ አገልግሎት መግለጫዎች ላይ ይታያል፡፡ ለምሳ፣ በ7፥15 ውስጥ፣ በፓለስቲኒያውያኑ የአይሁድ መሪዎች ፊት ሃይማኖትን ጠንቅቆ የማወቅን አስፈላጊነት አመልክቷል፡፡

የአራተኛው ወንጌል ጸሐፊ ከመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት የፓለስቲኒያ ጁዳይዝም ጽሑፎች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን መሪ ሃሳቦችና ቃላትንም ጠቅሷል፡፡ ለምሳሌ፣ በርካታ ምሁራን በዮሐንስ ወንጌልና በተለምዶ የሙት ባህር ጥቅል በሚባለው፣ በቁምራን፣ መካከል የቋንቋ ተመሳሳይነት እንዳለ አመልክተዋል፡፡ ለአብነት፣ “የብርሃን ልጆች” የሚለው አገላለጥ በቁምራን ዶኩሜንትም በዮሐንስ 12፥36 ውስጥም ይገኛል፡፡ “የሕይወት ብርሃን” የሚለውም ሐረግ በቁምራን ጽሁፎችም በዮሐንስ 8፥12 ውስጥም ይገኛል፡፡ እነዚህን የሚመስሉ መመሳሰሎች የሚያሳዩት የአራተኛው ወንጌል ጸሐፊ በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት ፓለስታይን ውስጥ ይደረጉ ከነበሩ ሃይማኖታዊ ወጎች ጋር ቤተኛ የነበረ መሆኑን ነው፡፡

የወንጌሉ ምንባብ በፓለስቲኒያዊ አይሁድ መጻፉን ብቻ ሳይሆን፣ የዐይን ምስክር በሆነ ሰውም የተጻፈ መሆኑን እንድናስተውል ያደርጋል፡፡ ይህም ከሐዋርያው ዮሐንስ ማንነት ጋር ይገጥማል፣ ምክንያቱም እርሱ ራሱ የኢየሱስ ሕይወት የዐይን ምስክር ነበርና ነው፡፡ ጸሐፊው የዐይን ምስክር የመሆኑን ማስረጃ በበርካታ ስፍራዎች እንመለከታለን፡፡ ለምሳሌ፣ ከኢየሱስ ሞት በኋላ፣ ዮሐንስ 19፥35 እንዲህ ይላል፡

> ***ያየውም መስክሮአል፤ ምስክሩም እውነት ነው፤ እናንተም ደግሞ ታምኑ ዘንድ እርሱ እውነት እንዲናገር ያውቃል።(ዮሐንስ 19፥35)***

በዚህ ስፍራ ፀሐፊው የኢየሱስ ሞት የዐይን ምስክር ስለመሆኑ በግልፅ ጽፏል፡፡ ተመሳሳዩንም በዮሐንስ 21፥20-24 ውስጥ የምናገኝ ሲሆን፣ “ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀመዝሙር” በሚል የዐይን ምስክሩን ገልጦታል፡፡ ይህም ጸሐፊው ከኢየሱስ ጋር የቀረበ ግንኙነት እንደነበረው ያሳያል፡፡

> **በጌታ ራት ወቅት ዮሐንስ ራሱን ወደ ኢየሱስ ደረት የማስጠጋቱ ነገር ለዮሐንስ ምን ሊሆን እንደሚችል እስኪ አስቡ፡፡ በእነዚህ ሁለት ሰዎች መሃል ስላለው ቅርብ ግንኙነትም አስቡ፡፡ በመስቀልም ላይ ኢየሱስ ሲሞት አንኳን፣ እናቱን አደራ የሰጠው ለወንድሞቹና ለእህቶቹ ሳይሆን ለሐዋርያው ዮሐንስ ነው፡፡ እንደገናም፣ በእነዚህ ሁለት ሰዎች መሃል በጣም የጠበቀ የቀርብ ግንኙነትም ይኖራል፡፡ ዮሐንስ ራሱን ኢየሱስ**

**የሚወድደው ደቀመዝሙር ብሎ ሲገልጥም፣ በትዕቢት እና በትምክህት አልነበረም፡፡ (ቄስ ታድ ጀምስ)**

ይህ "ኢየሱስ ይወድደው የነበረ ደቀመዝሙር" በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ደጋግሞ ተጠቅሷል፡፡ ለምሳሌ፣ ዮሐንስ 13፥23 እንደሚናገረው፣ የተወደደው ደቀ መዝሙር በመጨረሻዋ ራት ከጌታ አጠቀብ ተቀምጦ ነበር፡፡ በ19፥26-27 ውስጥ፣ ኢየሱስ ከመስቀል ላይ ይህን ደቀ መዝሙር ያናገረው ሲሆን፣ እናቱንም አደራ ሰጥቶታል፡፡ በ 20፥2-8 ውስጥ፣ ይኸው ደቀመዝሙር በትንሣኤ ማለዳ ከጴጥሮስ ጋር ወደ መቃብር ሮጧል፡፡ በ21፥7 ውስጥ ደግሞ፣ የተወደደው ደቀ መዝሙር በባህሩ ዳር ኢየሱስን የለየው የመጀመሪያ ሰው ነበር፡፡

**ሐዋርያው ዮሐንስ ራሱ በጻፈው ወንጌል ስሙ አንድም ቦታ አልተጠቀሰም ምክንያቱም ራሱን በኢየሱስ ከመወደዱ ጋር ብቻ ማጣቀሱን ምርጫው አድርጓልና ነው፡፡ ያንንም በማድረጉ፣ በአንድ በኩል ስብዕናውን በውል የገለጠ ወይም ሰውነቱን ያጋለጠ ሲሆን፣ በሌላ ጎኑ ደግሞ፣ ከጌታው ጋር በነበረው ግንኙነት የነበረውን ደስታ ያሳያል፡፡ ወንጌሉን ስታነቡ፣ የሌሎቹን ደቀ መዛሙርት ስሞች ሲጠቅስ የእርሱን ግን አለመጥቀሱ፣ በጣም የሚገርም ሆኖ ታገኙታላችሁ፡፡** (ቄስ ላሪ ኮክሬል)

በወንጌሉ ውስጥ ዮሐንስ በስም አንድ ጊዜ እንኳን አልተጠቀሰም፡፡ በሌሎቹ ወንጌላት ስሙ ደጋግሞ የተጠቀሰው ሰው በዚህኛው አለመጠቀሱ ያስገርማል፡፡ ለዚህ የሚስማማው መግለጫም ዮሐንስ ይህንን ወንጌል የጻፈ የተወደደው ደቀመዝሙር ነው፣ እናም ከትህትና በመነጨ መንገድ የራሱን ስም ከመግለጥ ታቅቧል፡፡ ይልቁኑ፣ አዳኙ ለእርሱ ካለው መለኮታዊ ፍቅር ውጪ የኢየሱስ ተከታይ ሊሆን የማይችል በመሆኑ እውነታ ላይ አትኩሯል፡፡

አራተኛው ወንጌል በራሱ ጸሐፊው ዮሐንስ ለመሆኑ ብርቱ ማስረጃ ቢያቀርብም ቀደምት የቤተክርስቲያን ጽሑፎችም ይህንን ድምዳሜ ያረጋግጣሉ፡፡

***ቀደምት ቤተክርስቲያን***

አራተኛው ወንጌል በሐዋርያው ዮሐንስ ተጽፏል የሚለው ድምዳሜ በቤተክርስቲያን ውስጥ ከ170 እስከ 190 ዓ.ም. ባሉት ዘመናት ይበልጥ ተረጋግጧል፡፡ የአሌክሳድሪያዎቹ ክሌመንት፣ ተርቱሊያን እና ኢራኒየስ ሁሉም በአንድነት ጸሐፊው፣ የዘብዴዎስ ልጅ፣ ዮሐንስ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ በ325 ዓ.ም. አካባቢ የቤተክርስቲያን ታሪክ ምሁር የሆነው ኢዮሲበስ *Ecclesiastical History* ከተሰኘው የኢራኒየስ 5፣11ኛ መጽሐፍ ክፍል 4 ውስጥ የሚከተለውን ጠቅሷል፡

**ከዚያም ዮሐንስ፣ የጌታ ደቀመዝሙር፣ በእርሱ ደረት ላይ ተጠግቶ የነበረው፣ ያው ሰው፣ በእስያዋ ኤፌሶን በነበረበት ወቅት አራተኛውን ወንጌል ጽፎልናል፡፡**

ቢያንስ በሁለት ምክንያቶች የኢራኒየስ ምስክርነት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ ኢዮሲበስ እንደተናገረው፣ ኢራኒየስ የስምርናው ሊቀጳጳስ፣ የፖሊካርፕ፣ ደቀመዝሙር ነበር፡፡ የሊቀ ጳጳሳቸውን መሰዋት አስመልክቶ ከስምርና በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት፣ ፖሊካርፕ ራሱ የሐዋርያው ዮሐንስ ደቀመዝሙር ነበር፡፡ ስለዚህም፣ ኢራኒየስ ዮሐንስን በግል ከሚያውቀው

ከታመነ ሰው ዮሐንስ ስለ መጻፉ ተረድቷል ማለት ነው፡፡ ሁለተኛ፣ በጥንታዊቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ፣ ኢራኒየስ በስፋት ይጓዝ ነበር፣ ስለዚህም ስለ አራተኛው ወንጌል ጸሐፊ ማንነት ጥሩ ፍንጭ ሊሰጡት የሚችሉ በርካታ መረጃዎችን ያገኝ ነበር፡፡

የዮሐንስን ጸሐፊነት በግልፅ የሚቃወም አለመኖሩም ሌላው ወሳኝ ነገር ነው፡፡ ከጥንት ቤተክርስቲያን ጽሑፎች በየትም ስፍራ ውስጥ ይህን ከዘብዴዎስ ልጅ፣ ከዮሐንስ ሌላ ሌላ ሰው ስለመጻፉ ሃሳብ ያቀረበም የለም፡፡ እንዲያውም፣ ታሪክ የመዘገበው በዮሐንስ ወንጌል ላይ ተቃውሞ ያላቸው ሁለት ቡድኖችን ብቻ ነው፡፡ እነርሱም፣ አሎጋውያንና መቃባውያን ናቸው፡፡ እነርሱም የዮሐንስን ወንጌል አስተምህሮ ቢቃወሙም፣ ጸሐፊነቱን ስለ መካዳቸው ግን በግልፅ አይታወቅም፡፡

ምንም እንኳን ይህ ሙሉ ስምምነት የተደረገበትን የወንጌሉ ጸሐፊ ማንነት ጉዳይ አስመልክቶ ሊኖሩ ከሚችሉ ጥርጣሬዎች ባሻገር ያለውን ሁሉ ማረጋገጥ የማይቻል ቢሆንም፣ ጸሐፊው ሐዋርያው ዮሐንስ ነው የሚለው ትውፊት ግን አሳማኝ ሆኖ ይዘልቃል፡፡

አራተኛውን ወንጌል ዮሐንስ ጽፎታል የሚለውን ትውፊት ከመረመርን እና አሳማኝም መሆኑን ካየን፣ አሁን ደግሞ የዮሐንስን የግል ታሪክ እንመልከት፡፡

## ግለ ታሪክ

ስለ ሌሎቹ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ከምናውቀው በበለጠ ስለ ዮሐንስ ይበልጥ እናውቃለን፡፡ ዮሐንስ በወንጌላት ውስጥ ከወንድሙ ጋር "የዘብዴዎስ ልጆች" በመባል ይታወቃል፡፡ ዮሐንስ በተጨማሪም በሁለተኛነት ተጠቅሷል፣ ያም የሚያመለክተው ታናሽ መሆኑን ነው፡፡ እንደ ማርቆስ 1፥14-21 አገላለጥ፣ የቤተሰቡ የዓሳ ማጥመድ ንግድ የሚገኘው በቅፍርናሆም አቅራቢያ በገሊላ ባህር ላይ ነው፡፡ እንደ ቁጥር 20 አባባል፣ ንግዱ የሚያዋጣና ሌሎች ተቀጥረው የሚሠሩበትም ነው፡፡ ከኢየሱስ ሞት በኋላ፣ ዮሐንስ 21፥1-14 እንደሚነግረን ተመልሰው ቢሄዱበትም የንግዱ አዋጪነት ብርቱ ነበር፡፡

በንጽጽሩ ማርቆስ 15፥40 እና ማቴዎስ 27፥56 ስንመለከት የእናታቸው ስም ሰሎሜ ሲሆን ቢያንስ ሁለት ጊዜያት ኢየሱስን ከሚከተሉት ጋር ተመዝግባለች፡፡ አንድ ጊዜ ደግሞ ልጆቿ በመንግሥቱ ውስጥ ልዩ አድልዎ እንዲደረግላቸው መጠየቋን ማቴዎስ 20፥20 ይነግረናል፡፡ ጥቂት ገፋ አድርገን፣ ዮሐንስ 19፥25 እና ማቴዎስ 27፥56 ስናነፃፅር ሰሎሜ፣ የዘብዴዎስ ልጆች እናት፣ የኢየሱስ እናት የማርያም እህት ነበረች፡፡ ይህም ዮሐንስን የኢየሱስ የአክስት ልጅ ያደርገዋል፡፡ ይህም እውነት ከሆነ በዮሐንስ 19፥25-27 ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሳለ እናቱን ለዮሐንስ ለምን አደራ እንደሰጠ ለማብራራት ያስችለናል፡፡

በማርቆስ 3፥17 ውስጥ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ "የነጎድጓድ ልጆች" ተብለዋል፡፡ ይህም ቁጡኝነታቸውን የሚያሳይ መግለጫ ነው፡፡ አንዱን ለምሳሌ ብናነሳ፣ ኢየሱስ በሳምራውያን ከተማ አንድ ሌሊት ማሳለፍ የፈለገበትን ወቅት ሉቃስ ዘግቦልናል፡፡ ነዋሪዎቹ ኢየሱስንና ደቀ መዛሙርቱን ማደሪያ

ሲከለከሏቸው፣ ያዕቆብና ዮሐንስ በብርቱ ተቆጥተው ነበር፡፡ በሉቃስ 9፥54-56 የተጻፈውን አድምጡ፡፡

> **ደቀ መዛሙርቱም ያዕቆብና ዮሐንስ አይተው። ጌታ ሆይ፥ ኤልያስ ደግሞ እንዳደረገ እሳት ከሰማይ ወርዶ ያጥፋቸው እንል ዘንድ ትወዳለህን? አሉት። እርሱ ግን ዘወር ብሎ ገሠጻቸውና። ምን ዓይነት መንፈስ እንደ ሆነላችሁ አታውቁም፤**
> **የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፉ አልመጣም አለ። ወደ ሌላ መንደርም ሄዱ። (ሊቃስ 9፥54-56)**

ከኢየሱስ ጋር በነበረባቸው ወቅቶች፣ የዮሐንስ ስሜት ግንፍል እያለ ይታይ እንደነበረና ድንገት ለመፈንዳትም አፍታ ብቻ የሚበቃው ይመስላል፡፡ ይህ ሰው በእግዚአብሔር ፍቅርና በእግዚአብሔር ህዝብ ፍቅር ላይ አትኩሮ የጻፈ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊ የመሆኑ ነገር አስገራሚ ነው፡፡

የአራተኛው ወንጌል ርኅራኄን የተላበሰ ገፅታ በሌሎች ወንጌላት ከተገለጠው የዮሐንስ አቋም ጋር የሚቃረን መሆኑን አንዳንድ ተቃውሞዎች ይገልጣሉ፡፡ እነዚህ ሁለት የአስተሳሰብ መስመሮች ግን ምንም ተቃርኖ የሌለ መሆኑን ግልፅ ያደርጋሉ፡፡ በመጀመሪያ፣ የዮሐንስ ታሪክ በእግዚአብሔር ፍቅር የተለወጠ ሰው ታሪክ ነው፡፡ በኢየሱስ መወደዱ ዮሐንስን ወደ ፍቅር ሐዋርያነት ለውጦታል፡፡ ሁለተኛ፣ እግዚአብሔር ግልፍተኛውንና ስሜታዊውን ዮሐንስ ሲለውጠው ስሜት አልባ የሰው ዘር አላደረገውም፡፡ እንዲያውም የፍቅር ወንጌል ሰባኪ ብርቱ ስሜታዊ ሰው ነው ያደረገው፡፡ የማንቱን መሠረት ለውጦ ተጠቀመበት እንጂ ማንነቱን አላጠፋውም፡፡

በወንጌላት ትረካ ውስጥ፣ ዮሐንስ ከጴጥሮስና ከያዕቆብ ጋር የኢየሱስ የቅርቦቹ ከሆኑት ወገን ነበር፡፡ እነርሱ ብቻ ወሳኝ በሆኑት ጊዜያት ማለትም በመለወጥ ተራራ እና በተያዘባት ሌሊት በጌተሰማኒ ጸሎቱ ወቅት እነርሱ ብቻ አብረውት ነበሩ፡፡ በሐዋርት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ሁለቱ የደቀመዛሙርት መሪዎች ነበሩ፡፡ በገላትያ 2፥9 ውስጥ፣ ጳውሎስ ዮሐንስን ከኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ምሰሶዎች አንዱ ብሎታል፡፡

በቀደመችው ቤተክርስቲያን፣ ኢራኒየስና ሌሎች በርካታ ምንጮች ዮሐንስ ከኢየሩሳሌም ከወጣ በኋላ በኤፌሶን ስለነበረው የረጅም ጊዜ አገልግሎት ዘግበዋል፡፡ በስተመጨረሻውም ዮሐንስ ወደ ፍጥሞ ደሴት በግዞት እንደተወሰደ የሚነገር ብርቱ ትውፊት አለ፡፡ እንደ አንዳንድ ምንጮች አገላለጥ፣ ከግዞት ተለቅቆ ወደ ኤፌሶን ተመልሷል፣ በንጉሥ ትራጃን ዘመን፣ በአንደኛው ምዕተ-ዓመት ማብቂያ ላይም ሞቷል፡፡

አራተኛውን ወንጌል ዮሐንስ እንደ ጻፈው የሚናገረውን ትውፊት ከተመለከትን፣ ከዮሐንስ ግለ ታሪክም ጋር በጥቂቱ ከተዋወቅን፣ የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈበትን ወቅት እንመልከት፡፡

# ወቅት

የዮሐንስ ወንጌልየተጻፈበትን ወቅት በአራት መንገዶች እንመረምራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የተደራሲያኑንና የጸሐፊውን መልክዓ-ምድራዊ አድራሻ እናስቀድማለን፡፡ ሁለተኛ፣ የቀደምት ተደራሲያኑን ማንነት በበለጠ ጥልቀት እንመረምራለን፡፡ ሦስተኛ፣ የተጻፈበትን ቀን እንመለከታለን፡፡ አራተኛ፣ ስለ ወንጌሉ ዓላማ እናስባለን፡፡ የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈበትን አድራሻ በመመልከት እንጀምር፡፡

## አድራሻ

ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው ኤፌሶን በነበረበት ወቅት ይመስላል፣ ስለዚህም የጻፈው ከፓለስታይን ውጪ፣ እንዲያውም በትንሿ እስያ ውስጥ ለሚኖሩ ተደራሲያን ነው፡፡ እነዚህን ነገሮች በእርግጠኝነት ባናውቅም፣ እነዚህን ድምዳሜዎች የሚያጸኑልን በርካታ ምክንያቶች ግን አሉን፡፡ ለምሳሌ፣ ዮሐንስ ስለ ፓለስታይን አይሁዳዊ ወጎች የሰጠው ማብራሪያ ከፓለስታይን ውጪ የሚኖሩ ተደራሲያንን ያመለክታል፡፡ በዮሐንስ 4፥9 ዮሐንስ የጻፈውን አድምጡ፡

> ***ስለዚህ ሳምራዊቲቱ። አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ መጠጥ እንዴት ትለምናለህ? አለችው፤ አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበርና። (ዮሐንስ 4፥9)***

በዚህ ጥቅስ ውስጥ፣ በሳምራውያንና በአይሁድ መካከል ስለነበረው ጠላትነት ዮሐንስ ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡ ይህ ጠላትነት በፓለስታይን በሚኖሩ ሰዎች በውል ይታወቃል፣ ስለዚህመ የዮሐንስ ማብራሪያ ተደራሲያኑ በሌላ ስፍራ የሚኖሩ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ወንጌሉ በተቀዳሚነት ከፓለስታይን ውጪ ለሚኖሩ ህዝቦች የተጻፈ ስለመሆኑ የቀደመችው ቤተክርስቲያን ጽሑፎችም ሃሳብ ያቀርባሉ፡፡ ይህን ወንጌል ዮሐንስ በትንሿ እስያ በምትገኘው በኤፌሶን ውስጥ በነበረ ወቅት እንደጻፈው ኢዮሲበስ ከኢራኒየስ ያጣቀሰውን ቀደም ብለን ዐይተናል፡፡ ኢራኒየስ፣ ፖሊካርፐ፣ የእስክንድርያው ክሌመንት እና መስዋዕቱ ጀስቲንን ጨምሮ ሁሉም የቀደምት ቤተክርስቲያን ጸሐፍት ከዚህ ድምዳሜ ጋር ይስማማሉ፡፡ ከዚያም ባሻገር፣ ከእነዚህ በትንሿ እስያ ከሚኖሩ ባሻገር ሌላ የመልእክቱ ተቀባይ ሊኖር እንደሚችል ያመለከተ አንድም ጥንታዊ ምንጭ የለም፡፡

በተጨማሪም በዮሐንስ ወንጌልና በራእይ መጻሕፍት መካከል ጥብቅ ቁርኝት አለ፡፡ ዮሐንስ የራእይን መጽሐፍ ጽፏል፣ ተደራሲያኑም በእርግጠኝነት በትንሿ እስያ የሚኖሩ ናቸው፡፡ በራእይ 2-3 የተጻፈው ደብዳቤ አድራሻ ያደረጋቸው ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉም በትንሿ እስያ የሚገኙ ናቸው፡፡ በዮሐንስ ወንጌል እና በራእይ መካከል ያሉት አስገራሚ ጉድኝቶች ተመሳሳይ ተደራሲ ነበራቸው የሚያሰኝ ጠንካራ መሠረት ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ፣ የዮሐንስ ወንጌል ወደ ክርስትና በተለወጡ እና በአይሁድ ምኩራቦች መካከል ከነበረው ግጭት ጋር የሚዛመዱ በርካታ

ትምህርቶችን ያቀርባል፡፡ የራእይ መጽሐፍም ለዚህ ችግር እውቅና ይሰጣል፡፡ በራእይ 2፥9 እና 3፥9 ጌታ ለቤተክርስቲያኑ የተናገረውን አድምጡ፡

> ***መከራህንና ድህነትህን አውቃለሁ፥ ነገር ግን ባለ ጠጋ ነህ፤ የሰይጣንም ማኅበር ናቸው እንጂ አይሁድ ሳይሆኑ። አይሁድ ነን የሚሉት የሚሳደቡትን ስድብ አውቃለሁ።… እነሆ፥ አይሁድ ሳይሆኑ። አይሁድ ነን ከሚሉ ነገር ግን ከሚዋሹ ከሰይጣን ማኅበር አንዳንዶችን እሰጥሃለሁ እነሆ፥ መጥተው በእግሮችህ ፊት ይሰግዱ ዘንድ እኔም እንደ ወደድሁህ ያውቁ ዘንድ አደርጋቸዋለሁ። (ዮሐ 2፥9፤3፥9)***

በተለየ አተያይ ደግሞ፣ ቢያንስ እስከዚያን ዘመን ድረስ የዮሐንስ ደቀመዛሙርት በኤፌሶን እንደነበሩ ከሐዋርያት *ሥራ* 19፥1-7 እንረዳለን፡፡ ሐዋርያው ዮሐንስ የመጥምቁ ዮሐንስም ተከታዮች ለተካተቱበት ተደራሲያን ከጻፈ፣ ወንጌሉ መጥምቁ ዮሐንስ ራሱን የኢየሱስ የበታች ለማድረጉ የሰጠውን አጽንዖት የበለጠ ግልፅ ያደርግልናል፡፡

ምንም እንኳን በጉዳዩ እርግጠኛ መሆን ባይቻልም፣ ዮሐንስ ወንጌሉን ሲጽፍ በኤፌሶን እንደነበረና በትንሿ እስያ በነበረው ሁኔታ የተቀነበበ ይመስላል፡፡

ወንጌሉ የተጻፈበት አድራሻ ኤፌሶን ሊሆን እንደሚችል ሃሳብ ካቀረብን፣ ዮሐንስ የጻፈላቸውን ቀደምት ተደራሲያን ባህርይ በበለጠ ጥልቀት እንመልከት፡፡

## ተደራሲያን

እንደ ሌሎቹ ወንጌላት ሁሉ፣ የዮሐንስ ወንጌልም በየዘመናቱ የምትመጣዋንም ቤተክርስቲያን ዒላማው የሚያደርግበትም መንገድ አለ፡፡ ለእግዚአብሔር ህዝብ በጠቅላላ የማይገደብ እሴት አለው፡፡ ሆኖም ከዮሐንስ ወንጌል አንዳንድ ክፍሎች በአንድ የተወሰነ ወቅትና ስፍራ ለነበረች ቤተክርስቲያን ለየት ያለ አግባብነት ያላቸውም አሉ፡፡ ቢያንስ በወንጌሉ ክፍሎች ውስጥ፣ ኢየሱስ መሲህ መሆኑን ያመኑ፣ ግን በምኩራብ አምልኳቸውን የቀጠሉ ወይም ከአይሁድ ማኅበረሰብ ጋር ጉልህ የሆነ ግንኙነት ያላቸውን የአይሁድ ማኅበረሰብ አማኞች በልቡናው አድርጎ ነበር፡፡ እንዲያውም የወንጌሉ ማዕከላዊ ክፍል በጠቅላላ ማለትም ከ5 እስከ 12 ያለው፣ በኢየሱስና በአይሁድ መካከል ስለነበረው ብርቱ ግጭት የሚያወሳ ነው፡፡

ዮሐንስ ከ70 ጊዜ በላይ የተጠቀመበት በሦስቱ ወንጌላት በአንድነት ግን ከ20 ጊዜ በታች የተገለጠው "**አይሁድም**"፣ በሚለው *ሃረግ* ጉዳዩን አስምሮበታል፡፡ በአብዛኛዎቹ ጊዜያት ዮሐንስ ይህንን አባባል የተጠቀመው የኢየሱስ ባላንጣ አድርገው ራሳቸውን ያስቀመጡትን የሃይማኖት መሪዎች ለማመልከት ነው፡፡

በንፅፅር፣ ዮሐንስ በአዎንታዊ መንገድ ስለ ብሉይ ኪዳኑ የእግዚአብሔር ህዝብ ሲናገር፣ “እስራኤል” ወይም “እስራኤላውያን” የሚሉትን ቃላት ተጠቅሟል፡፡ ለምሳሌ፣ በዮሐንስ 1፥48 ውስጥ፣ ኢየሱስ ናትናኤልን “ተንኮል የሌለበት በእውነት የእስራኤል ሰው” ብሎ ጠርቶታል፡፡

ከየትኛውም የወንጌላት ጸሐፊ በበለጠ ክርስቶስ የሚለውን የግሪክ ቃል ዮሐንስ ተጠቅሟል፡፡ “ክርስቶስ” የሚለው ቃል በግሪኩ *Christos* የተሰኘውና በእብራይስጡ *Mashiach* የተሰኘው ቃል ፍቺ ሲሆን፣ የሁለቱም ትርጉም የተቀባ ማለት ነው፡፡ ክርስቶስ እስራኤልን ከኃጢአትና ከባዕድ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት በእግዚአብሔር የተቀባ ቤዛ ነው፡፡

“ክርስቶስ” የሚለው ቃል በተለይ ለአይሁድ ክርስቲኖች እጅግ ወሳኝነት አለው ምክንያቱም በምኩራብና እያደገች በመጣችው የክርስቲያኗ ቤተክርስቲያን መካከል ያለው ልዩነት ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን የተተነበየለትና ሲጠበቅ የነበረው የእግዚአብሔር ህዝብ አዳኝ ነው የሚለው እምነት ነው፡፡

> ***የኋላ ኋላ፣ የአይሁዱ መሲህ “መሲህ” በሚለው ቃል ብቻ ተወስኖ እንደሚመጣ ብቻ ይቆጠር ነበር፡፡ ግን የሴቲቱ ዘር ሰይጣንንና ዝርያውን ሁሉ ድል የመንሳቱ ተስፋ ገና በዘፍጥረት 3፥15 በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ከመጀመሪያው አንስቶ በቀጣዮቹ ዓመታት ሁሉ፣ የሴቲቱ ዘር፣ በኋላ ደግሞ የአብርሃም ዘር፣ ቀጥሎ ደግሞ ከይሁዳ ወገን እንደሚሆን ተስፋ ተሰጥቷል፡፡ በእነዚህም ተስፋዎች እባቡ እንደሚፈረድበት፣ በአብርሃምና በዘሩ አማካይነት ደግሞ አህዛብ እንደሚባረኩ እና ከይሁዳም ደግሞ የገዢነት በትር ከእግሩ እንደማይርቅ ተነግሯል፡፡ እነዚህም ተስፋዎች በስተመጨረሻው በበለዓም ምርቃት ውስጥ በአንድነት ተያይዘው ቀርበዋል፡፡ ይህም እግዚአብሔር ገና ከጅማሬው፣ መሲሁ ከፉን ድል እንደሚነሳ፣ ወደ ኤድን ገነት የሚያስገባውንም በር እንደገና እንደሚከፍት እና በመጨረሻው ውሃ ባህርን እንደሚከድን የያህዌ ክብር የደረቀውን ምድር እንደሚሸፍን እግዚአብሔር ፕሮግራም ያደረገ መሆኑን ረጋግጣል፡፡*** (ዶ/ር ጀምስ ሃሚልተን)

ዮሐንስ የዳሰሳቸው ርዕሶችና የዳሰሰባቸው መንገዶች ተቀዳሚ ተደራሲያኑ የኢየሱስ ተከታዮች በመሆናቸው በትግል ውስጥ የነበሩት አይሁድ ክርስቲያኖች መሆናቸውን ያሳየናል፡፡ ሆኖም እንደ ሌሎቹ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ፣ የዮሐንስም መጽሐፍ በየዘመናቱ በምትመጣዋ ቤተክርስቲያንም አገልግሎት እንዲሰጥ የመንፈስ ቅዱስ ሃሳብ ነው፡፡ እንዲያውም በዮሐንስ 1፥42 እና 4፥25 ውስጥ፣ “መሲህ” የተሰኘውን የዕብራይስጥ ቃል ዮሐንስ ለአህዛብ ተደራሲያኑ ሲል ፍቺውንም አስቀምጧል፡፡ ታሪክም እንዳረጋገጠው የዮሐንስ ወንጌል ለአይሁድም ሆነ ለአህዛብ አማኞች ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡

ወንጌሉ የተጻፈበትን ወቅትና ተደራሲያኑን ከተመለከትን፣ እስኪ የተጠናቀረበትን ቀን እንመልከት

## ***ቀን***

በጥቅሉ፣ ዮሐንስ የጻፈው በ85 እና በ90 ዓ.ም. ማካከል ባለው ጊዜ ነው ማለት እንችላለን፡፡ ወንጌሉ ከ85 ዓ.ም. በፊት እንዳልተፃፈ የሚያሳዩ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ በመጀመሪያ፣

በ70ዓ.ም. የሆነውን የኢየሩሳሌምን መፍረስ ትንቢት ያላካተተ ዮሐንስ ብቻ ነው፡፡ ምናልባት ይህ የሆነበት ምክንያት መቅሰፍቱ ከተፈፀመ ረዘም ያለ ጊዜ ስላለፈ ይሆናል፡፡

ሁለተኛ፣ ወንጌሉ በቤተክርስቲያንና በምኩራብ መካከል መለያየቱ የመረረበትን ወቅት ያንፀባርቃል፡፡ ከኢየሩሳሌም መውደቅ በኋላ፣ ይሁዲነት ይበልጥ ግትር ሆነ፡፡ በየቀኑ ይደረግ የነበረው የምኩራብ ጸሎት ከኑፋቄ ራሱን ለመከላከል ሲባል በመናፍቃኑ ላይ ርግማንን እንዲጨምር ተደርጎ ተስተካክሎ ነበር፡፡ እርግማኑም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብለው የሚያምኑትን ይጨምራል፤ በይፋ ማውገዝም ደግሞ ደጋግሞ ይደረግ ነበር፡፡ ይህም ውጥረት ኢየሱስ የፈወሰውን ዕውር ሰው የወገዙበትን በዘገበበት እንደ ዮሐንስ 9 ባሉ ምዕራፎች ውስጥ አስቀድሞ እንዲታይ ተደርጓል፡፡ በዮሐንስ 9፥22 ውስጥ ስለሁኔታው የዘገበውን አድምጡ፡

> ***እርሱ ክርስቶስ ነው ብሎ የሚመሰክር ቢኖር ከምኵራብ እንዲያወጡት አይሁድ ከዚህ በፊት ተስማምተው ነበርና። (ዮሐንስ 9፥22)***

በዚህ ምንባብ፣ ከምኩራብ መውጣት ማለት ከአይሁድ ማኅበረሰብ ሕይወት መገለል እና ጨርሶውኑ መወገድ ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ፣ የዮሐንስ ወንጌል ከሌሎቹ ሦስት ወንጌላት በኋላ የተጻፈ ይመስላል፡፡ ይህ አመለካከት ወደ አራተኛው ክፍለ ዘመን የታሪክ ተመራማሪ ወደ ኢዮሲቢስ ይዘልቃል፡፡ እንደ እርሱ አባባል፣ ዮሐንስ በሌሎቹ ያልተዳሰሰውን ማሟላት የወንጌሉ ዓላማ እንዲሆን አድርጓል፣ በተለይም መጥምቁ ዮሐንስ ከመያዙ አስቀድሞ ባለው የኢየሱስ አገልግሎት ላይ አትኩሯል፡፡ እስኪ ኢዮሲቢስ *Ecclesiastical History*, በተሰኘው ሦስተኛ መጽሐፉ፣ 24 ክፍል 12 ላይ የጻፈውን አድምጡ፡

> **ዮሐንስ በወንጌሉ፣ መጥምቁ ወደ ወህኒ ከመጣሉ አስቀድሞ የተከናወኑ የክርስቶስን ሥራዎች የዘገበ ሲሆን፣ የጠቀሱት ሦስቱ ወንጌላውያን ግን ከዚያ በኋላ የተከናወኑትን ጠቅሰዋል፡፡ (ኢዮሲቢስ - *Ecclesiastical History*)**
>
> ***አራቱን ወንጌላት የሚያነብብ የትኛውም ሰው ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ በጣም የሚመሳሰሉ ሦስት ወንጌላት መሆናቸውን በቶሎ ያስተውላል፤ በርካታ ተመሳሳይ ታሪኮች ይዘዋል፤ ከኢየሱስ አገልግሎት አንፃርም መሠረታዊ አወቃቀርን ይከተላሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ግን፣ ፍፁም ልዩ የሆነውን አራተኛውን ወንጌል፣ የዮሐንስን ወንጌል ታገኛላችሁ፡፡ የዮሐንስ ወንጌል በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት ማብቂያ ግድም፣ ቤተክርስቲያን ከውጪው ዓለም፤ ከአይሁድ ባላንጣዎች እና ከዓለማውያን ተቃውሞ በገጠማት ወቅት የተጻፈ ይመስላል፡፡ እነዚህም ተግዳሮቶች በአንድ ወገን በእርግጠኝነት የሚያያዙት በኢየሱስ ማንነት ላይ ነው፡፡ የክርስቶስ አምላክነት እሳት እየነደደበት ያለ ነገር ነበር ምክንያቱም የዮሐንስ ወንጌል አፅንዖት የሰጠው፣ ኢየሱስ በእውነት መለኮት ነው በሚለው ላይ ነበር፡፡ ለሦስቱ ወንጌላት ግን ዋና ጉዳይ አልነበረም፣ ምክንያቱም ተግዳሮቱ በዚያን ወቅት አልነበረምና ነው፡፡ ሌላው ደግሞ፣ በዚያን ወቅት በቤተክርስቲያን ውስጥ የስህተት ትምህርት እያቆጠቆጠ ነበርና የዮሐንስም ወንጌል ለዚያ***

**የስህተት ትምህርት ምላሽ የሚሰጥ ይመስላል፡፡ ሦስተኛው ነገር፣ የአይሁድ ተቃዋሚዎች ጉዳይ ሲሆን፣ በሌሎቹ ሦስት ወንጌላት በማቴዎስ፣ በማርቆስ እና በሉቃስ በሙላት የማናስተውለው ልዮነት በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እናየዋለን፡፡ (ዶ/ር ማርክ ስትራውስ)**

እነዚህ ሁሉ ነገሮች የሚመሩን ወንጌሉ የተጻፈው በዮሐንስ የመጨረሻ የሕይወት ምዕራፍ ምናልባትም ከ85 ዓ.ም. በኋላ ነው የሚለው ጥንታዊ የቤተክርስቲያን ትውፊት ትክክል ነው ወደሚለው ድምዳሜ ነው፡፡ የዚህ ወንጌል ጸሐፊ የዘብዴዎስ ልጅ፣ ዮሐንስ ከሆነ፣ ወንጌሉ የተፃፈበት የመጨረሻው ወቅት ሊወሰን የሚችለው በእርሱ የዕድሜ እርዝማኔ ነው፡፡ ዮሐንስ በ30 ዓ.ም. ገደማ፣ ኢየሱስን መከተል ሲጀምር ገና ወጣት ነበር፡፡ ምንም እንኳን ዮሐንስ በዚያን ወቅት በዐሥራዎቹ ዕድሜ ማብቂያ ላይ ቢሆንም፣ በ90 ዓ.ም. የ80 ዓመት ሰው ይሆናል፡፡ ከዚያን የበለጠ ኖሯል የሚለው በጣም አጠራጣሪ ነው፡፡

ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈበት የኋለኛው ዘመን 85 ወይም 90 ዓ.ም. ነው የሚለው ሃሳብ ከጥንታዊ ጽሑፎች ማስረጃ ጋር ይስማማል፡፡ የአዲስ ኪዳንን የተወሰነ ክፍል የያዘው ጥንታዊው ጽሑፍ ፓፒረስ 52 የተሰኘውና በተጨማሪም *Rylands Papyrus* ተብሎ የሚጠራው ነው፡፡ ይህ ቅሪተ መድብል የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 18 ከፊል ክፍል ይዟል፡፡

ፓፒረስ 52 በ100 እና በ150 ዓ.ም. መካከል እንደተጻፈ ይነገራል፡፡ ይህ ትንሽ ቁራጭ አስቀድሞ ሙሉውን ወንጌል ይዞ ነበር ብለን ብናስብ፣ በሁለተኛው ምዕተ-ኣመት ጅማሬ ላይ በአግባቡ በስፋት ይሰራጭ ዘንድ ወንጌሉ ቀደም ብሎ መጻፍ ይኖርበታል፡፡ በሁለተኛው ምዕተ-ዓመት ማብቂያ አካባቢም የወንጌሉ ሌሎች ጥንታዊ ጽሑፎች ተገኝተዋል፡፡ እነዚህም ጽሑፎች ሁሉም የግብጻውያን ሲሆኑ፣ የተለያዩ የጥንታዊ ጽሑፍ ትውፊቶችን ይወክላሉ፡፡ ከትንሿ እስያ እስከ ግብጽ ያለውን መልክዓ ምድራዊ ርቀት ያካተተ ጉዞና የጥንታዊ ጽሑፎች ትውፊት ልዮነት ያለበት ሂደት ከ40 ወይም ከ50 ዓመት በታች ወሰደ ማለት አጠራጣሪ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈበት የመጨረሻው የኋለኛ ዘመን 90 ወይም 100 ዓ.ም. ነው ማለት አሳማኝ ነው፡፡

የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈበትን አድራሻ፣ ተደራሲያኑንና ዘመኑን ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈበትን ዓላማ እንዳስሳለን፡፡

## ዓላማ

መጠነ ሰፊ የሆኑት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ በርካታ ዓላማዎች አሏቸው፣ የዮሐንስ ወንጌልም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ኢየሱስ በአገልግሎቱ ዘመን በርካታ ርዕሰ ጉዳዮችን እንደዳሰሰ ሁሉ፣ ስለ ኢየሱስ አገልግሎት ዮሐንስ ያቀረበው ዘገባም በርካታ ርዕሶችን ይዳስሳል፡፡ እነዚህን ዓላማዎች በተቀናጀ መንገድ ማቅረብም ደግሞ ይቻላል፡፡ በመሠረቱ፣ ዮሐንስ ዓላማዎቹን ጠቅለል አድርጎልናል፡፡ በተለይም ደግሞ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆኑን እምነት ሊያረጋግጥ እንደሚፈልግ ተናግሯል፡፡ እስኪ በዮሐንስ 20፥30-31 ምን እንደጻፈ አድምጡ፡፡

> ***ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፤***
> ***ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥***

***አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል።***
***(ዮሐንስ 20፥30-31)***

በቀላሉ ስናስቀምጠው፣ ተደራሲያኑ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ መሆኑን እንዲያምኑና ይህንንም የወንጌል መልእክት በማመን የሚገኘውን በረከት እንዲቀበሉ ስለፈለገ ዮሐንስ ጽፏል፡፡

> **በእርግጥም፣ ወንጌሉን ከጻፈበት ምክንያት አንፃር ዮሐንስ የተለየ ነው፡፡ በዮሐንስ 20፥31 ውስጥ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንድናምን፣ በማመናችንም በእርሱ የዘላለምን ሕይወት እንደምናገኝ ለማመልከት እነዚህ ነገሮች እንደተጻፉ አመልክቷል፡፡ በዚያ ስፍራ የተገለጠው ሁለት ዓላማ ያለው ነገር ነው፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ በመጀመሪያ፣ ወንጌሉ በተፈጥሮው ወንጌላዊ ነው፡፡ በግልጽ እንደተቀመጠው፣ በሆነ ወቅት ላይ አንባቢዎቹ፣ ጌታ ወደ ራሱ ሲስባቸው፣ በእርሱ ያምኑ ዘንድ ነው የጻፈው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ዐቃቤያዊ ተፈጥሮም አለው፡፡ ኢየሱስ በእርግጥ ሰው-የሆነው አምላክ ስለ መሆኑ አንባቢዎቹን ሊያሳምናቸውም ይፈልጋል፡፡ (ቄስ ላሪ ኮክሬል)**
>
> **ዮሐንስ እያለ ያለው፣ ይህንን ወንጌል የምጽፈው የኢየሱስን ማንነት እንድታውቁ ነው፡፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ይልና የእግዚአብሔር ልጅ ማን መሆኑን ያብራራል፡፡ እርሱ ከአብ ጋር የነበረ እና ስጋ የሆነ ቃል ነው፣ ኢየሱስ እርሱ በተስፋ የተነገረው መሲህ ነው ይህም ዝም ብለን ወደላይ መጥቀን የምናቀብላችሁ ስውር መረጃ አይደለም፣ ይልቁኑ በእርሱ በአስተማማኝነት ልታምኑበት የሚገባ ከዚያም የተነሳ አብ በእርሱ አማካይነት የሚሰጣችሁን ሕይወት የምትቀበሉበት ነው፡፡ (ዶ/ር ሮበርት ፕሉመር)**

በወንጌሉ በጠቅላላ፣ የዮሐንስ ዓላማ ማዕከላዊ ትኩረት ኢየሱስ መሲህና የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለውን እምነት ማስተዋወቅ ነው፡፡ እነዚህም አይሁድ ክርስቲያኖች በምኩራብ በሚገጥማቸው ግጭት ወቅት በጣም የሚያግዟቸውና የሚያስፈልጓቸው ሁለት ነገሮች ናቸው፡፡ ኢየሱስን እርሱ ክርስቶስ እና የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ሊያምኑ፣ ደግሞም የድነትን በረከት ይቀበሉ ዘንድ ያንኑ እምነት አጽንተው ሊይዙ ይገባቸዋል፡፡

የዮሐንስ ወንጌል ለሁሉም አማኞች እንደሆነም የምንረዳበት መንገድ አለ፡፡ ለምሳሌ፣ በዮሐንስ 13-17 ውስጥ ኢየሱስ ምንም እንኳን አሁን በምድር ባይመላለስም፣ በህዝቡ ሕይወት ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የአሁን ዘመን እውነታ መሆኑን አጽንዖት በመስጠት የአማኞችን ሕይወት ያነቃቃል፡፡ ሁሉም የዮሐንስ ትምህርቶች የአማኞችን ሕይወት ማጠንከርን ዒላማ ያደረገ ነው፡፡

ምሁራኑ፣ የዮሐንስ ወንጌል "ሕፃናት የሚንቦጫረቁበት ዝሆኖች የሚዋኙበት ገንዳ ነው" ይላሉ፡፡ መሠረታዊ መልእክቱ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚል ቀላልና ግልፅ ነው፡፡ የእነዚህ መሠረታዊ መልዕክቶች ዝርዝር ግን ወንጌሉን ለዓመታት ላጠኑ ተርጓሚዎች ፈተና ሆነው ቀጥለዋል፡፡

ይህን ወንጌል ያነበቡ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በጥልቀት ተበረታትተውበታል፡፡ ከተቃዋሚዎቻቸው በሚገጥማቸው ጦርነት ሳይሸበሩ በክርስትና እምነታቸው ጸንተው እንዲዘልቁ አስተምሯቸዋል፡፡ የተትረፈረፈ ሕይወት ብቸኛ ምንጫቸው ለሆነው ለክርስቶስ ባላቸው ፍቅርና አክብሮት እንዲያድጉም ይሞግታቸዋል፡፡ የዮሐንስ ወንጌል ለዘመኑም ክርስቲያኖች እነዚህኑ ተመሳሳይ ማበረታቻና ሙግት ያቀርብላቸዋል፡፡

የዮሐንስን ወንጌል ዳራ ካጠናን፣ አሁን ደግሞ ወደ ወንጌሉ ውቅርና ይዘት እንሸጋገር፡፡

# 3. ውቅርና ይዘት

ምሁራኑ የዮሐንስን ወንጌል ውቅር በተለያዩ መንገዶች ይገልፁታል፡፡ በዚህ ትምህርት፣ በኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት ላይ በቀረበው የዮሐንስ የመግቢያ ጥቅል ሃሳብና በዮሐንስ መጽሐፍ ይዘት መካከል ግንኙነት እንዳለ የሚያመለክቱትን በመከተል እንመለከታለን፡፡ በዮሐንስ 1፥10-14 የተጻፉትን እስኪ አድምጡ፡

> *(ኢየሱስ)በዓለም ነበረ፥ ዓለሙም በእርሱ ሆነ፥ ዓለሙም አላወቀውም።*
> *የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም።*
> *ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤*
> *እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።*
> *ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን። (ዮሐ 1፥10-14)*

ይህ ምንባብ በአራት ዋና ሃሳቦች ማለትም፡ ኢየሱስ ወደ ዓለም በመምጣቱ፤ ወደ ገዛ ህዝቡ በተለይም እስራኤል፣ በመምጣቱ እነርሱ ግን ያልተቀበሉት በመሆናቸው፤ እርሱን ያመኑና የተቀበሉት የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናቸው፤ እነዚህም አማኞች የኢየሱስ ምስክሮች በመሆናቸው ላይ ያተኩራል፡፡

እነዚህን አራት ሃሳቦች በመከተል፣ የዮሐንስን ወንጌል በዚህ መንገድ እናዋቅረዋለን፡

- በመጀመሪያ፣ በ1፥1-18 ውስጥ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ትሥጉት አጭር መግቢያ በመስጠት ወንጌሉን ይከፍታል፡፡
- ሁለተኛ፣ በ1፥19-12፥50 ውስጥ ዮሐንስ ወደገዛ ፍጥረቱ እንደመጣና በሰውም ዘር እንደተናቀ ያሳየበትን የኢየሱስን የአደባባይ አገልግሎት ይዘግባል፡፡
- ሦስተኛ፣ በ13፥1-20፥31 ኢየሱስ እርሱን ለተቀበሉና ላመኑ የሰጠውን የብቻ አገልግሎት ማብራሪያ ዮሐንስ ያቀርባል፡፡

* አራተኛ፣ በ21፥1-25 በዮሐንስ ወንጌል ማጠቃለያ ውስጥ፣ የሐዋርያትና የሌሎች ደቀመዛሙርት ሃላፊነት የኢየሱስ ክብር ምስክር መሆን መሆኑን ላይ ዮሐንስ አፅንዖት ሰጥቶበታል፡፡

ከመግቢያው ጀምረን እነዚህን የዮሐንስን ወንጌል ክፍሎች እንመለከታለን፡፡

# መግቢያ

ዮሐንስ ወንጌሉን ጠቅለል አድርጎ በ1፥1-18 ውስጥ ውብና ብርቱ አድርጎ አቅርቦታል፡፡ ኢየሱስ እርሱ ሁሉን የፈጠና የሕይወት ሁሉ ምንጭ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አስተምሯል፡፡ ከዚህ በበለጠ ግን፣ ኢየሱስ ሥጋና ደም ያለው እውነተኛ ሰው ሆኖም ወደ ዓለም መጥቷል፡፡ እናም እንደ ትስጉተ-እግዚአብሔር፣ ለፈጠረው ዓለም የአብን ክብር ገልጧል፡፡

ዮሐንስ ይህንንም በ1፥4-5 ውስጥ ኢየሱስ ወደ ጨለማው ዓለም የመጣ ብርሃን በማለት ገልጦታል፡፡ ጨለማውንም ያሸነፈው የእግዚአብሔር ጸጋ ምሉዕ መገለጫ በመሆን ነው፡፡ በትስጉቱ ወራት የኢየሱስ ክብር ተሸፍኖ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ጊዜ ቢናገርም፣ የኢየሱስ ትስጉት ወሳኝ በሆነ መንገድ ክብሩ እንዲታወቅ የማድረጉን እውነታ ዮሐንስ አስምሮበታል፡፡ ስለዚህ ሰው መሆኑ የኢየሱስን ክብር ከመጋረድ ይልቅ ክብሩን ገልጧል፡፡ ዮሐንስ በ1፥14 ውስጥ እንዲህ ጽፏል፡

> ***ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን። (ዮሐንስ1፥14)***

መግቢያውን ተከትሎ፣ ከ1፥19-12፥50 ዮሐንስ የኢየሱስን የአደባባይ አገልግሎት መዝግቧል፡፡ በዚህ ክፍል፣ ኢየሱስ ወደ ገዛ ወገኖቹ፣ ወደ እስራኤል፣ በመምጣቱና የእስራኤልም ህዝብ ኢየሱስን እንደ ክርስቶስና ጌታ ለመቀበል ባለመፍቀዳቸው ላይ አተኩሯል፡፡ በዮሐንስ 1፥11 ውስጥ እንደምንመለከተው፣ ዮሐንስ እንዲህ ብሏል፡

> ***የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። (ዮሐ 1፥11)***

በዚህ ማጠቃለያ ውስጥ ወሳኝ የሆኑ ለየት ያሉ ነገሮች ቢኖሩም፣ የእስራኤል ህዝብ የኢየሱስን የአደባባይ አገልግሎት እንዴት ምላሽ እንደሰጡት ጠቅለል አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡

ስለ ኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት የምናደርገው ዳሰሳ በሰባት ክፍሎች ይከፈላል፣ ለአገልግሎት ካደረገው ዝግጅት ይጀምርና፣ በስድስቱ የተለያዩ የአይሁድ በዓላት ዙሪያ የተከናወኑትን ያስከትላል፡፡ በመጀመሪያ በ1፥19-2፥12 ውስጥ ኢየሱስ ለአደባባይ አገልግሎት ባደረገው ዝግጅት እንጀምር፡፡

## ለአገልግሎት መዘጋጀት

ይህ ኢየሱስ ለአገልግሎት ያደረገው ዝግጅት የተመዘገበበት ክፍል የሚጀምረው በ1፥19-36 በመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ነው፡፡ በዚህ ምንባብ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ፣ የዓለምንም ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር የመስዋዕት በግ ስለመሆኑ መጥምቁ ዮሐንስ በሰጠው ምስክርነት ላይ ዮሐንስ አፅንዖት ሰጥቷል፡፡

ይህንንም ተከትሎ፣ የኢየሱስን የመጀመሪያ ደቀመዛሙርት መጠራት በ1፥37-51 ውስጥ ዮሐንስ ዘግቧል፡፡ እንደ መጥምቁ ዮሐንስ አባባል፣ የዚህ ክፍል አፅንዖት በኢየሱስ ማንነት ላይ ነው፡፡ በቆጥር 38 ውስጥ፣ ደቀመዛሙርቱ "ረቢ" ሲሉት ትርጓሜውም "መምህር"፤ በቁጥር 41፣ "መሲህ" ትርጌሜውም ክርስቶስ፤ በቁጥር 45፣ "ሙሴ ስለ እርሱ የጻፈለት" ማለትም ነቢዩ ሙሴ አስቀድሞ የተነበየለት፤ በቁጥር 49፣ "የእግዚአብሔር ልጅ" ተዛማጁ ቃልም "የእስራኤል ንጉሥ"፤ በመጨረሻም በቁጥር 51 ውስጥ፣ ኢየሱስ ራሱን "የሰው ልጅ" ማለትም ወደ እግዚአብሔር ጎላዊ ያስገባን ዘንድ የተላከ በማለት ጠቅሶታል፡፡

ኢየሱስ ለአገልግሎት ያደረገው ዝግጅት የመጨረሻ ክፍል የተዓምራቱ መጀመሪያ የሆነውና በዮሐንስ 2፥1-12 የተመዘገበው ነው፡፡ ይህም ኢየሱስ ውሃውን ወደ ወይን የለወጠበት ነው፡፡ ትኩረቱ ግን በተዓምራቱ ላይ አልነበረም፡፡ በ2፥11 ውስጥ ዮሐንስ ምን እንደጻፈ አድምጡ፡

> ***ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ። (ዮሐ 2፥11)***

ዮሐንስ ማስቀመጥ የፈለገው አንዱ ነጥብ ይህ ተዓምር የኢየሱስን ክብር የሚገልጥ ምልክትና ደቀመዛሙርቱ በእርሱ እንዲያምኑ ያደረገ መሆኑን ነው፡፡

> **"ምልክት" የሚለው ቃል ሙሴ ያደረጋቸውን ተዓምራት የሚጠቅስ በዘፀአት መጽሐፍ የተጠቀሰ ቃል ሲሆን፣ በተለይም ለመቅሰፍቶቹ የዋለ ይመስለኛል፡፡ እናም ምልክቶች ወይም "ምልክት" የሚለው ቃል ተዓምራትን ለማመልከት አገልግሎት ላይ ውሏል ማለት ነው፡፡ እናም ዮሐንስ ደጋግሞ ኢየሱስን ከሙሴ ጋር ሲያነፃፅረው ማለት የፈለገው ልክ የዘፀአቱ ጸሐፊ ሊያስተላልፍ እንደፈለገው ሁሉ ተዓምራቶች የሚከናወኑት ለሰዎች አንድ ነገር ለማሳየት፣ እነርሱም እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸውን ነገር ለማሳሰብና መረጃ ለመስጠትም ልትሉት ትችላላችሁ፣ በተለይም እግዚአብሔር ለህዝቡ አንድ ነገር ሊናገርና እነርሱም ምላሽ እንዲሰጡት ሊያሳስብ የሚደረጉ መሆናቸውንም ለማመልከት ነው፡፡ (ዶ/ር ዴቪድ ሬድሊንግስ)**

የኢየሱስን ተዓምራት *"semeion"*፣ አዘውትሮ "ምልክቶች" ተብሎ እንደሚተረጎመው በመጥቀስ ዮሐንስ ከሌሎቹ ወንጌላት ይለያል፡፡ የተዓምራቱ ዓላማ ትኩረትን ወደ ራሳቸው መሳብ ሳይሆን፣ ከእነርሱ ባሻገር ወደ ኢየሱስ ለማመልከት ነው፡፡ በተለይም ዮሐንስ በ20፥30-31 ዓላማውን

ጠቅለል አድርጎ እንዳቀረበው፣ ኢየሱስ እርሱ “ክርስቶስ” “የእግዚአብሔር ልጅ” ለማመልከት ነው፡፡

> **በርካታ ሰዎች የኢየሱስ ተዓምራት ተጠቃሚዎች ሆነዋል፣ ሆኖም ግን ሊያመለክቱዋቸው ወደ ፈለጉት ወደ ክርስቶስ ማንነት ማየት የቻሉት ግን ዐይኖቻቸው የተከፈቱላቸው ብቻ ነበሩ፡፡ ስለዚህም ዮሐንስ ተዓምራት የሚለውን ቃል ሲጠቀምና ስለ ተዓምራት ሲናገር፣ ስለ አስደናቂ ተዓምራዊ ወቅቶች ለመናገር ፈልጎ ሳይሆን፣ ወደ ክርስቶስ ማንነት ለማመልከት ሊጠቀምባቸው ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ እንዲያውም የጻፍሁላችሁ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ስለ መሆኑና ያንንም በማመን በስሙ ስለ ምታገኙት ሕይወት እንድታውቁ እና ምልክቶቹም የዚያን ተግባር ክንዋኔ የሚገልፁ መሆናቸውን ነው፡፡ (ዶ/ር ሲሞን ቫይበርት)**

> **ምልክት ኢየሱስ እውነተኛ ማንነቱን ለማመልከት የሚያከናውነው ነገር ነው፡፡ የዐይነ ስውሩን መፈወስ ቢሆን፣ አምስት ሺዎችን በተዓምር መመገቡን ቢሆን፣ ወይም ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጡን ቢሆን እንዲያው በቁሳዊ ነገር ላይ የተመሠረተ ድንቅ ሥራ ብቻ አድርጋችሁ ከወሰዳችሁት ዋናውን ነገር ትስቱታላችሁ፡፡  በጠቅላላው የዮሐንስ መጽሐፍ ውስጥ፣ ዮሐንስ እነዚህን ነገሮች እንደ ተዓምራዊ ሥራዎች ብቻ አያያቸውም፣ እነዚህን ግን እግዚአብሔር በዓላማ እንደሚያከናውናቸው ነገሮች ካያችሁዋቸው፣ የኢየሱስን ማንነት እውነተኛ መገለጥ፣ ማለትም የሕይወት እንጀራ መሆኑን ታያላችሁ፡፡ እርሱ ብርሃንን ሊሰጠን፤ አዲሱንም የወይን ጠጅ ይዞልን የመጣ ነው እኛም በዚያ ደስ ይለናል፡፡  (ዶ/ር ሮበርት ፕሉመር)**

## የመጀመሪያው ፋሲካ

ስለ ኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት የሚናገረው ሁለተኛው ክፍል በኢየሩሳሌም በተከበረው የፋሲካ በዓል አካባቢ የተከናወነው ነው፡፡ ይህንንም እንደ መጀመሪያው ፋሲካ እንጠቅሰዋለን ምክንያቱም በዮሐንስ ወንጌል ተለይቶ በስም የተጠቀሰ የመጀመሪያው ነውና፡፡ ይህም ክፍል በዮሐንስ 2፥13-4፥54 ውስጥ ይገናል፡፡

ይህ ክፍል የሚጀምረው በዮሐንስ 2፥13-20 ኢየሱስ ነጋዴዎችን ከመቅደስ ስለ ማባረሩ ዮሐንስ ባቀረበው ዘገባ ነው፡፡ እናም በድጋሚ፣ ትኩረቱ የኢየሱስ ማንነት ነው፡፡ በዮሐንስ 2፥18 አይሁድ ኢየሱስን ምን እንደጠየቁት እስኪ አድምጡ፡

> ***ስለዚህ አይሁድ መልሰው። ይህን ስለምታደርግ ምን ምልክት ታሳየናለህ? አሉት። (ዮሐ 2፥18)***

ኢየሱስ መልስ የሠጠው ስለ ራሱ ሞትና ትንሣኤ አስቀድሞ በመናገር ነው፣ ያም እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆኑ ከሚያረጋግጡ ምልክቶች ሁሉ የላቀው ነው፡፡

በ2፥21-25 በሚገኘው፣ ከዚህ ዘገባ በኋላ በሰጠው አስተያየት፣ ኢየሱስ ሌሎች በርካታ ምልክቶችን ማሳየቱን እና በውጤቱም ብዙዎች በውጫዊ መንገድ ቢሆንም እንኳን በስሙ ማመናቸውን ዮሐንስ ይጠቅሳል፡፡

ከዚያም፣ በ3፥1-21 ውስጥ፣ ኢየሱስ ከኒቆዲሞስ፣ የአይሁድ የአመራር ሸንጎ አባል ጋር ስላደረገው አስገራሚ ንግግር ይዘግባል፡፡ እንደገናም፣ በዚህ ወቅት አፅንዖት የተሰጠው ኢየሱስ “የሰው ልጅ” እና “የእግዚአብሔር ልጅ” በሆነው ማንነቱ ላይ እና ሊፈፅፈው በተላከበት ዓላማ ላይ ነበር፡፡

በዮሐንስ 3፥22-36 ውስጥ፣ የመጥምቁ ዮሐንስን ሌላ ታሪክ እናገኛለን፡፡ በዚህኛው ውስጥ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ያስተጋባል፡፡ ኢየሱስ የመጣው ስለ መዳንና ስለ እግዚአብሔር ሊመሰክር ነበር፣ አብዛኛው ሰው ግን በእምነት አልተቀበለውም ነበር ያለው፡፡

በዮሐንስ 4፥1-42 ውስጥ፣ ኢየሱስ በሰማርያ ከሳምራዊቷ ጋር ስላደረገው ንግግር ዮሐንስ ዘግቧል፡፡ አንድ ጊዜ በድጋሚ፣ አፅንዖት የተደረገበት ኢየሱስ እርሱ መሲሁ፣ ወይም ክርስቶስ ሁሉን ለህዝቡ ሊገልጥ የመጣው መሆኑ ነበር፡፡ ድነት በአይሁድ በኩል እንደሚመጣ፣ በተለይም በእርሱ በኩል እንደሆነ በመንገር አስተሳሰቧን የሞገተው ሲሆን፣ ዘወትርም ስትፈልገው የነበረውን ሕይወትና የእግዚአብሔር እውነታ እንድታገኘው ጥሪ አቀረበላት፡፡ በርካታ ሳምራውያንም በእርሱ በማመን ለትምህርቱ ምላሽ ሰጡ፡፡

በመጨረሻ፣ በዮሐንስ 4፥43-54 ውስጥ፣ የኢየሱስን ታምራዊ ምልክት ዮሐንስ ዘግቧል፡፡ እንደ መጀመሪያው ምልክት ሁሉ፣ ይህኛውም የተከናወነው በቃና ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ግን ኢየሱስ ልጁን የፈወሰው ሳያየው ወይም ሳይነካው ነበር፡፡ የዚህም ታሪክ አፅንዖት ተዓምሩ የኢየሱስን ሥልጣን ዋጋ ለመስጠትና የሚመሰክሩለትንም ወደ እምነት ለማምጣት ነበር፡፡

በመጀመሪያው ፋሲካ፣ በክፍሉ ውስጥ ዳር እስከ ዳር የሚዘልቀው አንድ ወሳኝ ዐቢይ ርዕስ እምነት ነው፡፡ ከመጀመሪያው ተዓምር በኋላ፣ ደቀመዛሙርቱ በእርሱ ማመናቸውን፣ በ2፥11 ውስጥ፣ ከኢየሱስ ትምህርቶች የተነሳ ሳምራውያን ማመናቸውን፣ በ4፥42 ውስጥ፣ የተፈወሰው ልጅ ቤተሰቦች ማመናቸውን፣ በ4፥53 ውስጥ፣ ወደ ኋላ ደግሞ፣ በ7፥50 እና በ19፥39 ውስጥ፣ ኒቆዲሞስም እንዳመነ እንድናስብ የሚያደርገንን ምክንያት እናገኛለን፡፡ የኢየሱስ ምልክቶች እና ጽኑ ትምህርቶቹ ስለ ማንነቱና ስለሚያስገኘውም ድነት ብርቱ ምስክሮቹ ናቸው፣ ከዚህም የተነሳ በርካቶች አምነውበታል፡፡

> **በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ከሚገኙት ዐቢይ ርእሶች መካከል አንዱ ለድነት የሚያበቃ እምነት ነው፤ ማመን የወንጌሉ አጠቃላይ አፅንዖት ነው፡፡ ትኩረቱም በሁለት አካባዎች ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ አንዱ ማመን ወይም የእግዚአብሔር ልጅ መሆን፣ የእግዚአብሔር የራሱ ሥራ ነው፣ የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ፣ ተግባራዊ ምላሽ ነው፡፡ አንድ ሰው ለድነት የሚያበቃው እምነት በእርግጥ ስጦታ መሆኑን ማወቅ ይገባዋል፣ ማመንም የቻልነው በሕይወታችን ከተቀመጠው የእግዚአብሔር ጸጋ የተነሳ ነው፣ ሆኖም እኛም የምንወስደው እርምጃ አለ፣ ያም ከእውቀት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ክርስቶስ ስለ**

ኃጢአታችን በመስቀል ላይ መሞቱን መረዳት ይገባናል፡፡ ከዚያም ጋር መስማማታችንን በብርቱ መግለፅ ይገባናል፡፡ ነገሩ ግን ከማወቅና ከመስማማት የዘለለ ነው፡፡ በውስጡም የመታመን ነገር ሲኖርበት፣ ያም የእምነት ወሳኝ ክፍል ነው፡፡ በጥቅሉ እግዚአብሔር በልጁ በክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር የሠራለትን ሥራ ለመቀበል ባዶ እጁን የዘረጋ ሰው እጅ ነው ማለት ነው፡፡ (ዶ/ር ጆፍ ሎውማን)

ታውቃላችሁ፣ በዙሪያችን ባለው ዓለም በጣም አሳዛኝ ከሆኑት ሁሉ የሚልቀው “እምነት” የሚለው ቃል ነው፡፡ ይህ ቃል እንዳልባሌ እና በግድየለሽነት አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡ ከእምነት ከራሱ ውስጥ እምነት እናገኛለን ብለው የሚናገሩ በርካታ ሰዎች አሉ፡፡ ክርስቲያኖች ስለ እምነት የሚናገሩት ግን በዚያ መንገድ አይደለም፡፡ የተለያዩ የእምነት አይነቶች አሉ፡፡ አሁን እኔ በወንበር ላይ ተቀምጫለሁ፡፡ እኔን ሊያስቀምጠኝ እንደሚችል፣ ተማምኜበታለሁ፡፡ በወንበሩም አምኜበታለሁ፡፡ ሆኖም፣ እኔን ከማስቀመጥ የዘለለ ነገር እንዲያደርግልኝ የምጠብቅበት እምነት ግን የለኝም፡፡ ሌላም ዓላማ የለውም፡፡ ስለ ሚያድነው እምነት ስንነጋገር ግን፣ በክርስቶስ ላይ ያለ እምነት ነው፡፡ ያም ክርስቶስ ለድነታችን የሚስፈልገውን ሁሉ እንዳደረገልን ማመንና ማረፍ ነው፡፡ የሚያድነው እምነት ማለትም በክርስቶስ ያለን እምነት ክርስቶስ የኃጢአት ዕዳችንን የከፈለ፣ ክርስቶስ ድነትን ያስገኘልን፣ ክርስቶስ ለኃጢአታችን ምሉዕ ስርየትን ያስገኘልን፣ በእርሱም የኃጢአትን ይቅርታ ሙሉ በሙሉ ያስገኘልን መሆኑን ማወቅን ይጠይቃል፡፡ የሚያድን እምነት በክርስቶስ በትልቅ መተማመን የማመንና የማረፍ፣ ያንንም በእኛ ምትክ እንዳደረገ፣ ገናም ሊሠራ የሚገባው የቀረ ነገር አለመኖሩን እና በእርሱ ያመኑትንም ለዘላለም የሚጠብቅ መሆኑን ማወቅ ነው፡፡ ታውቃላችሁ፣ የሚያድነው እምነት፣ በክርስቶስ መታመናችን በብቸኝነቱ እና እጅግ ወሳኝ በመሆኑ የሚገለጥ ነው፡፡ ከዚያ ሌላ ምንም የለንም፡፡ ከዚያ ሌላ ምንም አንመኝም፡፡ ለመዳናችን ክርስቶስ በቂ መሆኑን እናውቃለን፡፡ (ዶ/ር አልበርት ሞህለር፣ ትንሹ)

የሚያሳዝነው ግን፣ ሁሉም ሰው ኢየሱስን በእምነት አይቀበልም፡፡ በ2፥12-20 ውስጥ፣ መቅደሱን ያረከሱትን ኢየሱስ አባርሯል፡፡ በ2፥24-25 ውስጥ፣ ኢየሱስ በአብዛኞቹ ሰዎች አይተማመንባቸውም ነበር፣ ምክንያቱም እውነተኛ እምነት አልነበራቸውም ነበር፡፡ በ3፥18-21 ውስጥ ደግሞ፣ ማመንን አሻፈረኝ በሚሉ ላይ ስለሚመጣው ፍርድ እናነባለን፡፡

## ስም የለሽ በዓል

ሦስተኛው የኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት ክፍል በዮሐንስ 5፥1-47 ውስጥ የሚገኘውና ከስም የለሹ በዓል ጋር የተያያዘው ነው፡፡

ከቁጥር 1 እስከ 15 ውስጥ፣ ለ38 ዓመታት ያህል በተስፋ ቢስነት የተቀመጠውን ሰው ኢየሱስ ፈውሶታል፡፡ ሆኖም ቀኑ ሰንበት ስለነበር፣ በሰንበት ቀን በመሥራት ህግ ተላልፈሃል ተብሎ ኢየሱስ በአይሁድ ተወገዘ፡፡ ዮሐንስ በ5፥16-47 በእርሱ ላመኑ የዘላለምን ሕይወት እንደሚሰጥ የተናገረበትን የኢየሱስን ምላሽ ዘግቧል፡፡

## ሁለተኛው ፋሲካ

ስለ ኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት የሚያወሳው አራተኛው ክፍል በዮሐንስ 6፥1-40 የሚገኘውና ከሁለተኛው ፋሲካ አከባበር ጋር የተያያዘው ነው፡፡

ፋሲካ እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡበትን ቀን የሚያከብሩበት በዓል ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ክፍል ከዘፀአት መጽሐፍ በርካታ ማጣቀሻዎችን መያዙ አያስደንቅም ማለት ነው፡፡ በ6፥1-15 ውስጥ፣ ኢየሱስ በአምስት እንጀራና በሁለት አሦች አምስት ሺዎችን በተዓምር መግቧል፡፡ ይህ ተግባር እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት ከወጡ በኋላ ከእግዚአብሔር መና የተቀበሉበትን ወቅት የሚያሳስብ ነው፡፡

በዮሐንስ 6፥16-24 ውስጥ፣ ሙሴ ቀይ ባህርን ከከፈለበት ትዕዛዝ የሚልቅ ሥልጣን እንዳለው ለማሳየት ኢየሱስ በውሃ ላይ ተራምዷል፡፡ ከዚያም፣ በ6፥25-59 ውስጥ፣ ባህሩን ከተሻገረ በኋላ፣ ኢየሱስ ራሱን “ከሰማይ የመጣ እንጀራ” አድርጎ አቅርቧል፣ በዚህም በዘፀአት ወቅት እግዚአብሔር ከሰጠው መና እጅግ የሚልቅ መሆኑን አሳይቷል፡፡ እንደ እውነተኛ እንጀራ፣ ኢየሱስ ለሚያምኑ ሁሉ እውነተኛ ሕይወት የሚሰጥ ሆኖ የፋሲካን በዓል ፈፅሟል፡፡

## የዳስ በዓል

አምስተኛው የኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት ክፍል በዮሐንስ 7፥1-10፥21 በሚገኘው በዳስ በዓል አከባበር ዙሪያ የሚከናወን ነው፡፡

በዮሐንስ 7፥1-52 ውስጥ፣ ኢየሱስ እንዴት የዳስን በዓል እንዳከበረ ዮሐንስ ዘግቧል፡፡

በዮሐንስ 7፥1-52 ውስጥ፣ ኢየሱስ የዳስን በዓል ዓላማዎች አሟልቷል፡፡ የዳስ በዓል እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ነፃ ያወጣበት መታሰቢያ በዓል ሲሆን፣ በበረሃ ውሃ ያፈለቀላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ለመከር ዝናብ የመስጠቱን የእግዚአብሔር ቀጣይ በረከትም ያከብራል፡፡ እግዚአብሔር ወደፊት ህዝቡን ነፃ የሚያወጣበትን ቀንም ያመለክታል፡፡ በበዓሉ ወቅት፣ ካህኑ በመቅደሱ ውስጥ በመሰዊው ዙሪያ ውሃን በማፍሰስ የእግዚአብሔርን የቸርነት ስጦታ ያመለክታል፡፡ ኢየሱስም ይህንን የውሃ ምስላዊ መግለጫ በመጠቀም፣ እርሱ የ“ሕይወትን ውሃ” የሚሰጥ መሆኑን በድፍረት አውጇል፡፡

በዮሐንስ 8፥12-59 ውስጥ፣ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ በመጥራት እውነተኛውን ልጅነት ገልጧል፡፡ ኢየሱስ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ ጠርቷል፡፡ ያላመኑትን አይሁድ ግን የአብርሃም ህጋዊ ልጆች መሆናቸውን እንኳን ውድቅ አድርጎባቸዋል፡፡

በ9፥1-42 ውስጥ፣ ኢየሱስ የሚያደርገውን ነገር በጥንቃቄ ለሚመረምሩ ፈሪሳውያን ምላሽ ለመስጠት ሲል፣ ኢየሱስ ከመወለዱ ጀምሮ የማያይ የነበረውን ሰው ፈውሷል፡፡ አለማመናቸውም ፈሪሳውያን እናያለን ቢሉም እንኳን የታወሩ እንደሆኑ እንዲናገር አድርጎታል፡፡

በ10፥1-21 ውስጥ፣ ኢየሱስ ራሱን እንደ መልካም እረኛ አቅርቧል፡፡ ከፈሪሳውያን ተቃራኒ በሆነ መንገድ፣ ኢየሱስ ነፍሱን ስለ በጎቹ ለማኖር የሚፈቅድ መልካም እረኛ ነው፡፡

## የቤተመቅደስ መታደስ በዓል

የኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት ስድስተኛው ክፍል የተዘገበው በዮሐንስ 10፥22-11፥57 የቤተ መቅደሱን የመታደስ በዓል በማክበሩ ዙሪያ በሚያጠነጥነው ታሪክ ነው፡፡ ኢየሱስ የመቅደሱን የመታደስ በዓል እንዳከበረና እንደፈፀመው ዮሐንስ 10፥22-40 ዘግቦልናል፡፡

ይህ በዓል በብሉይ ኪዳን አልተመዘገበም፡፡ መከበር የጀመረው በ165 ዓመተ ዓለም፣ የካህናት ወገን የሆኑት መቃባውያን በግሪኩ ንጉሥ አንቲቆስ ኤፒፋኔስ ላይ የተሳካ አብዮት ካካሄዱ በኋላ ነበር፡፡ አንቲቆስ፣ ኤፒፋኔስ የሚለውን ማዕረግ የወሰደበት ምክንያት የአማልክት መገለጫ ነኝ ብሎ ስላመነ ነው፡፡ በርካቶችን በኢየሩሳሌም ጨፍጭፏል፣ መቅደሱን አርክሷል፣ አይሁድ ዜየስ የተባለውን ጣዖት እንዲያመልኩ አዝዟል፡፡ ስለዚህ የቤተ መቅደሱ መታደስ በዓል የመቅደሱ መንፃት የሚከበርበት ሲሆን ይህም የሆነው መቃባውያን እንደገና በመቀደስ ካስከበሩት በኋላ ነው፡፡ ዛሬ፣ በዓሉ በውል የሚታወቀው ሃኑካ፣ ማለትም “**የቤተ መቅደስ መታደስ**” በተሰኘው የዕብራይስጥ ስሙ ነው፡፡

ይህም ምንባብ ኢየሱስን ከአንቲቆስ ጋር በተቃርኖ ያመለክታል፡፡ በአንድ በኩል፣ አንቲቆስ የእግዚአብሔርን ህዝብ በመጨፍጨፍና መቅደሱን በማርከስ በሃሰት መለኮት ነኝ ብሎ ሲያውጅ፡፡ በሌላ ወገን ግን፣ ኢየሱስ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ የአባቱንም ሥራ በታማኝነት የሚያከናውን፣ ለህዝቡም የዘላለምን ሕይወት የሚሰጥ ነው፡፡ በዮሐንስ 10፥36 ውስጥ፣ ኢየሱስ እርሱ የተቀደሰ መሆኑን ወይም አንዳንድ ትርጉሞች እንደሚያስቀምጡት “ተቀድሶ ወደ ዓለም የተላከ” በማለት አውጇል፡፡ ይህም ቋንቋ በቤተ መቅደሱ የመታደስ በዓል ወቅት የመቅደሱን መቀደስ መልሶ አሳይቷል፡፡ እንዲያውም፣ በዮሐንስ 2፥19-21 ውስጥ፣ ኢየሱስ የመቅደሱን እንደገና መሠራት ከአካላዊው ትንሣኤው ጋር አስተያይቶታል፡፡

እነዚህም መሪ ሃሳቦች በዮሐንስ 11፥1-57 ወደተመዘገበው እና ኢየሱስ በሞት ላይ ያለውን መለኮታዊ ኃይል ወደሚገልጠው የአልዓዛር የትንሣኤ ታሪክ ይወስዱናል፡፡ የአልዓዛር ከሞት መነሣት በወንጌሉ ፍፃሜ የሚገለጠውን የኢየሱስን ትንሣኤ፣ ማለትም በመጨረሻ ሁሉም የመቅደሱ መታደስ ተስፋዎች በሙላት የሚፈፀሙበትን በጥላነት የሚያመለክት ነው፡፡

## ሦስተኛው ፋሲካ

የኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎት ሰባተኛው ክፍል የሚያጠነጥነው በዮሐንስ 12፥1-50 ውስጥ በተመዘገበው ለሦስተኛው ፋሲካ በተደረገው ዝግጅት ዙሪያ ነው፡፡

ዮሐንስ የጠቀሰው ይህ ኢየሱስ ለሦስተኛው ፋሲካ ያደረገው ዝግጅት ከምእራፍ 13-17 ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ለሰጠው አገልግሎትና በተጨማሪም በምዕራፍ 19 ለተገለጠውም እንደ ፋሲካ በግ ለሚቀርበውም መስዋዕትነቱ መድረኩን አመቻችቷል፡፡ የኢየሱስ ዝግጅት የጀመረው ለቀብሩ

በተቀባበት በ12፥1-11 ባለው ክፍል ነው፡፡ ከቁጥር 12 -19፣ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በድል መግባቱን ዮሐንስ ዘግቧል፡፡ በዮሐንስ 12፥20-50 ውስጥ፣ በሞቱና በትንሣኤው የሚከብርበት ሰዓት መሆኑን ኢየሱስ በአደባባይ አውጇል፡፡ የሚሰሙት በእርሱ እንዲያምኑም ኢየሱስ ጥሪ አቅርቧል፡፡ ግን በፊታቸው በርካታ ተዓምራትን እያደረገ እንኳን፣ ብዙ አይሁድ ቢያምኑም እጅግ በርካቶች ግን አላመኑም፡፡

ቀጣዩ የዮሐንስ ወንጌል ዐቢይ ክፍል የሚያወሳው እርሱን ለተቀበሉና ላመኑበት ኢየሱስ የሰጠውን አገልግሎት ነው፡፡ ይህ ክፍል ከዮሐንስ 13፥1-2031 ይዘልቃል፡፡

## ኢየሱስ ላመኑበት የሰጠው አገልግሎት

በዚህ የወንጌሉ ክፍል ዮሐንስ ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ስለበላው የመጨረሻ እራት፣ ስለ መያዙ፣ ስለ መሰቀሉ እና ስለ ትንሣኤው ዘግቧል፡፡ ኢየሱስ ለእርሱ ለተለዩ ሰዎች ክብሩን የገለጠበት ታሪክ ነው፡፡ ኢየሱስ በእርሱ ላመኑ ሰዎች የቅርበት አገልግሎት እንደሰጠና በፈቃዱም ሕይወቱን እንደሰጣቸው ዮሐንስ አስተምሯል፡፡ በእነዚህ ወቅቶች፣ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ መንገድ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ክብር ገልጧል፡፡

ይህ የዮሐንስ ወንጌል ክፍል ዮሐንስ በምዕራፍ 1፥11-12 ገልጦት የነበረውን ሃሳብ ገለጥለጥ የሚያደርግ ነው፡፡ በዚያም እንዲህ ጽፏል፡-

> ***የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም።***
> ***ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ (ዮሐ 1፥11-12)***

በዮሐንስ ወንጌል የመጀመሪያ 12 ምዕራፎች ውስጥ፣ ኢየሱስ ዓለምን ሁሉ አገልግሏል፣ ግን የራሱ የሆኑት እንኳን አልተቀበሉትም፡፡ ከዚያም፣ ከ13 ጀምሮ፣ በተቀበሉት ማለትም በደቀመዛሙርቱ ላይ አተኩሯል፡፡

ይህን የዮሐንስ ወንጌል ክፍል በሁለት ከፍለን እናየዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ በመጨረሻው እራት የነበረውን ሁኔታ እናያለን፡፡ ሁለተኛ፣ ኢየሱስ እጅግ የከበረበትን ሰዓት ማለትም፣ ሞቱንና ትንሣኤውን እንመለከታለን፡፡ እስኪ በመጨረሻዋ እራት ወቅት በሆኑት ነገሮች እንጀምር፡፡

## የመጨረሻው እራት

በመጨረሻዋ እራት ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው አገልግሎት በአራት ክፍሎች ይገለጣል፡፡ በመጀመሪያው ክፍል፣ በዮሐንስ 13፥1-30 ውስጥ፣ ኢየሱስ እግራቸውን በማጠብ አገልግሏቸዋል፡፡

*አገልግሎት*

ኢየሱስ የደቀመዛሙርቱን እግር ባጠበበት ወቅት የምድር አገልግሎቱን አጠቃላይ ተምሳሊት አሳይቷል፡፡ ይህ ሁኔታ ትስጉቱንና በመስቀል ላይ ለድነት የሚሆነውን መስዋዕትነቱን በጣምራ

በድራማ አሳይቷል፡፡ የፍጥረተ-ዓለሙ ፈጣሪ በራሱ ህዝብ ፊት በመንበርከክ የደከመና፣ ቁሽሽ ያለ እግራቸውን በማጠብ አገልግሏል፡፡ ይህም አገልግሎት በነጋታው በመስቀል ላይ በሚያፈስሰው የማንፃት ደሙ የደከመና የቆሸሸውን ነፍስ ሲያነፃ ወደ ከፍተኛው እርከን ይደርሳል፡፡ እግሮቻቸውን ካጠበ በኋላ፣ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ እንደሚሰጠው ኢየሱስ ይፋ አደረገ፡፡ ከዚያም ሰይጣን በይሁዳ ከገባበት በኋላ፣ አሳልፎ ሊሰጠው ክፍሉን ለቅቆ ወጣ፡፡

እግሮቻቸውን በማጠብ ደቀመዛሙርቱን ካገለገለ በኋላ፣ በ13፥31-14፥31 ውስጥ፣ ኢየሱስ አጽናንቷቸዋል፡፡

*ማጽናናት*

ይሁዳ ከሄደ በኋላ፣ በቶሎ የሚለያቸው የመሆኑን እውነታ ለታመኑት ደቀመዛሙርቱ በመናገር ያዘጋጀበትን፣ በተለምዶ "የመሰነባበቻ ንግግር" ተብሎ የሚጠራውን ንግግር ኢየሱስ ያደርግ ጀመረ፡፡

> ***ምንም እንኳን ታዳሚዎቹ ሐዋርያት ቢሆኑም፣ ጉዳዩ ቀጥሎ ለሚመጣው ሐዋርያዊ ትውልድ ተጠብቆ የቆየበት አንድ ምክንያት ይኖራል ብዬ በእርግጠኝነት አምናለሁ፡፡ በሌላ አባባል፣ እንደ ሐዋርያ ለመኖር ለሚያስብ እና ራሱን ለሚያለማምድ ሰው፣ በመማርም ላይ ላለ እና ወደ ዓለም መላኩን ለተረዳ ሰው የሚሆንም ተሺጋጋሪ መልእክት አለበት፡፡ ነገሩን በውል ከተረዳችሁት፣ በላይኛው ክፍል ውይይት ውስጥ አስደናቂ ትምህርቶች አሉበት፡፡ በዚያ ምንባብ ውስጥ ከመሪዎች ጋር በተለይ የሚዛመዱ ትምህርቶች አሉ፡፡ እንደማስበው በክርስቶስ አካል ውስጥ ወደ አመራር ስፍራዎች የሚመጡ ወንዶችና ሴቶች ሁሉ እነዚህን ምእራፎች ለላቀ ትርፍ ሊያነብቧቸው ይገባል፡፡ በመደበኛነት እያልኩ ያለሁት ግን የክርስቲያን ዓላማ ወይም ጭብጥ በጠቅላላው በዮሐንስ 17 በኢየሱስ ውስጥ ተገልጧል፣ ምክንያቱም እርሱ ጸሎቱን ሲከፋፍለው፣ እንደምታውቁት፣ ለሐዋርያቱ ከጸለየ በኋላ፣ ለእነዚህ ብቻ ሳይሆን፣ ከምስክርነታቸው የተነሳ ለሚያምኑት ሁሉ በማለት ተናግሯልና ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ በዮሐንስ 14፣15፣16 እና 17 ያሉ ክፍሎች በዐሥራሁለቱና እነርሱም ከሄዱ በኋላ በእግራቸው በተመሳሳይ ሃላፊነት ስለሚሰማሩት እያለዋወጡ የሚናገሩ ናቸው፡፡ ስለዚህ ክፍሉን ለአማኞች ሁሉ እንደ ሆነ ክፍል አየዋለሁ፡፡ (ዶ/ር ስቲቭ ሃርፐር)***

ኢየሱስ የመሰነባበቻ ንግግሩን የጀመረው የሚከብርበት ሰዓት መድረሱን በመናገር ነው፡፡ ማለትም፣ እንደሚሞት፣ ከሞት እንደሚነሣ እና በሰማይ ወዳለው አባቱ እንደሚያርግ ማለት ነው፡፡ በመካከላቸው እየተመላለሰ፣ እየተነጋገረ በአካል አብሯቸው የማይኖርበትን ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ሊጋፈጡት ነው ማለት ነው፡፡ ጴጥሮስም ሦስት ጊዜ እንደሚክደው አስቀድሞ ተናግሯል፡፡ እነዚህ አስቸጋሪ ዜናዎች ደቀመዛሙርቱን እንደሚያስጨንቋቸው ያውቃል፣ ስለዚህም አጽናናቸው ደግሞም በመጨረሻ እነርሱንም ወደ አብ እንደሚያመጣቸው አረጋገጠላቸው፡፡ ብቻቸውንም እንደማይተዋቸው፤ በእርሱ ምትክ ሆኖም እንዲያገለግላቸው መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው አረጋገጠላቸው፡፡ በዮሐንስ 14፥26 ኢየሱስ የሰጠውን ተስፋ አድምጡ፡፡

*አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል። (ዮሐንስ 14፥26)*

ደቀመዛሙርቱ ብቻቸውን እንደማይቀሩ ዮሐንስ ቃል ገብቶላቸዋል፡፡ በዓለም መከራን ቢቀበሉ እና ለፍርድ ቢቀርቡም፣ ሆኖም ለኢየሱስ ስም ብቻቸውን ተሟጋች ሊሆኑ አይችሉም፡፡ የእውነት መንፈስ እንደ ኢየሱስ ሆነው በሥልጣንና በማይሻር መንገድ እንዲናገሩና እንዲጽፉ ያስችላቸዋል፡፡

ደቀመዛሙርቱን ካጽናና በኋላ፣ ኢየሱስ በዮሐንስ 15፥1-16፥33 ውስጥ ለመሄዱ እና ወደፊት ለሚጠብቃቸው አገልግሎት አዘጋጃቸው፡፡

*ዝግጅት*

ቀደም ባለው ክፍል ማብቂያ ላይ፣ ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ የነበሩበትን ስፍራ ለቅቀው ሄዱ፣ ኢየሱስም አዲሱን ንግግሩን ጀመረ፡፡ በዮሐንስ 15፥1-8 ውስጥ፣ ራሱን እንደ "እውነተኛ የወይን ግንድ" በማስተዋወቅ ጀመረ፡፡ ተለዋጭ ዘይቤው እስራኤል በከበረው ወይራ ከተገለጠችበት ከመዝሙር 80፥8 እና ከኢሳያስ 5፥1-7 ያጣቀሰ ነው፡፡ እስራኤል ግን ከውድቀቷና ከበደሏ የተነሳ የኋላ ኋላ በኤርምያስ 2፥21 ውስጥ "ክፉ፣ እንግዳ ወይራ" ተብላ ተጠራች፡፡ ኢየሱስ ግን ይህንን ስዕላዊ መግለጫ በመጠቀም እውነተኛዋንና ታማኟን እስራኤልን ራሱ እንደሚመሠርታት እና እነርሱም የዚህ ትልቅ ዕቅድ አካል እንደሚሆኑ ለደቀመዛሙርቱ አረጋግጦላቸዋል፡፡ ኢየሱስ በዮሐንስ 15፥1-5 የተናገረውን አድምጡ፡

*እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤ … እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ፡፡ … በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል። (ዮሐንስ 15፥1-5)*

እውነተኛ የወይን ግንድ ነኝ በማለቱ፣ ኢየሱስ ትርጉም በሚሰጥ መንገድ፣ እርሱ ራሱ እስራኤል መሆኑን ተናግሯል፡፡ ኢየሱስ እስራኤልን በመወከል፣ የእስራኤልን ትክክለኛ ማንነት አመልክቷል፡፡ እስራኤል የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር መመሥረት አቃታት፣ ኢየሱስ ግን አሳካው፡፡ ደቀመዛሙርቱ ደግሞ የወይኑ ቅርንጫፎች ናቸው፡፡ እግዚአብሔር በየዘመናቱ ዕቅዱን የሚያስፈፅምባቸው ህዝቡ፣ አካል ነበሩ፡፡

ሆኖም ዓለም አስቀድማ እርሱን ስለጠላች፣ ደቀመዛሙርቱንም እንደምትጠላቸው ኢየሱስ ያውቃል፡፡ ስለዚህም፣ እነርሱ ወደ አብ በጸሎት የሚቀርቡበትን በር የከፈተላቸው መሆኑን አረጋግጦላቸዋል፡፡ እነርሱ የእርሱ አምባሳደሮች፣ በምድር ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴዎቹ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ኢየሱስ ራሱ እንደጸለያቸው ዓይነት አብ ጸሎቶቻቸውን ይቀበላል፡፡ በዮሐንስ 16፥23-24 እንዲህ ብሏቸዋል፡

*እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል። እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ። (ዮሐንስ 16፥23-24)*

ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ካዘጋጃቸው በኋላ፣ በዮሐንስ 17፥1-26 ውስጥ ስለ እነርሱ ጸለየ፡፡

*ጸሎት*

በዮሐንስ 17 የሚገኘው የኢየሱስ ጸሎት የሊቀ ካህንቱ ጸሎት በመባል ይታወቃል፣ ምክንያቱም ለተከታቹ እንደ ካህን ማልደ ልና ነው፡፡ በተለይም፣ አብ የእርሱን ደቀመዛሙርት እንዲጠብቃቸው ከዚያም የተነሳ ብዙዎች በእነርሱ አማካይነት እንዲያምኑ ኢየሱስ ጸልዮአል፡፡ ከዓለም ክፋት እነርሱና የእነርሱ ደቀመዛሙርት እንዲጠበቁ፣ አንድነታቸውም እንዲያበረታቸው እና ሕይወታቸውም እግዚአብሔርን እንዲያከብር ጸልዮአል፡፡

> **ኢየሱስ ጊዜው አጭር እንደሆነ፣ ይህም ጊዜ፣ እርሱ እንደተናገረውም፣ ዓለም ሳይፈጠር አንድ ወደነበሩበት ከአባቱ ጋር ለመሆን የሚመለስበት ጊዜ ነበር፡፡ እናም በዚህ ወቅት፣ ኢየሱስ በመጽሐፍ የተባለው ይፈፀም ዘንድ፣ ከአንዱ ከጥፋት ልጅ በስተቀር፣ የሰጠኸኝን ሁሉ ጠብቄአለሁ ብሏል፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ በእውነት የጸለየው ስለ ደቀመዛሙርቱ ነበር፣ ከ3 እስከ 3 ½ ዓመታት ለሚያህል ጊዜም ልቀድሳቸውና ወደዚህ ደረጃ ላደርሳቸው አብሬያቸው ሠርቻለሁ ሲል ተናግሯል፡፡ አሁን ግን፣ እኔ ከእነርሱ ጋር በዚህ አልሆንም፣ ስለዚህ አባት ሆይ፣ እባክህ ጠብቃቸው፣ ቀድሳቸውም ምክንያቱም እነርሱ በታላቅ መከራ ውስጥ ሊያልፉና በፍርድ ፊት ሊቀርቡ ነውና በዚያ ውስጥ እንዴት ሊያልፉ እንደሚገባቸው አሳያቸው፡፡ እናም እንደገና፣ ጸሎቱ ደቀመዛሙርቱን ከፊታቸው ለሚጠብቃቸው መከራ፣ ለስደቱ፣ ለመሰዋቱና የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለማዳረስ ለሚጠብቃቸው ሥራ ራሳቸውን እንዲሰዉ ለማዘጋጀት ለእግዚአብሔር የቀረበ ጸሎት ነበር፡፡ (ቄስ ታድ ጀምስ)**

ዮሐንስ የመጨረሻውን እራት ካብራራ በኋላ፣ በዮሐንስ 18፥1-20፥31 ውስጥ፣ የኢየሱስን ሞትና ትንሣኤ ይዘግባል፡፡

## ሞትና ትንሣኤ

በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ፣ የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ደግሞም ከእነርሱ ጋር የተያያዙ ክስተቶች ሁሉ ደጋግመው የሚገለጡት እንደ ኢየሱስ የመከበሪያ ሰዓት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ "ክብር" የሚለው ቃል የሚዛመደው እግዚአብሔር በህዝቡ መካከል ከመገኘቱ ጋር ነው፡፡ በእስራኤል ታሪክ ሁሉ ውስጥ፣ የእግዚአብሔር ክብር ከእስራኤል ጋር ነበር፡፡ ክብሩም እስራኤላውያን በምድረበዳ በሚንከራተቱበት ወቅት እንደ ደመና በላያቸው እንደነበረ በዘፀአት 16፥10 እናያለን፡፡ በዘፀአት 40፥34-35 ደግሞ፣ በመገኛኛው ድንኳን ውስጥ ነበር፡፡ በ1ኛ ነገሥት 8፥11 ደግሞ የእግዚአብሔር ክብር በሰሎሞን ቤተመቅደስ ላይ ወርዶ ነበር፡፡ ከዚህ ጋር በተገናኘ መንገድም፣ በዮሐንስ ወንጌል "ክብር" የሚለው ቃል የሚያጣቅሰው ትስጉተ እግዚአብሔር የሆነውን ኢየሱስን ነው፡፡ ሆኖም ኢየሱስ "የምከብርባት ሰዓት" ብሎ ሲናገር፣ በሕይወቱ ውስጥ ስለምትገኘውና ክብሩንም ጽኑ በሆነ መንገድ ለዓለም ሁሉ ስለሚገልጥባት ስለ አንድ የተለየች ወቅት እየተናገረ ነው፡፡ በሌላ አባባል፣ ስለ ሞቱና ስለ ትንሣኤው እየተናገረ ነበር፡፡

ሞት ክብር እንዳለበት በመደበኛ ሁኔታ አናስበውም፡፡ የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ግን ለእግዚአብሔር ህዝብ እርቅን አስገኝቷል፡፡ በፈቃዱ ራሱን መስዋዕት ማድረጉና ትንሣኤው ለማኑበትን እንደ መሲህ ለተቀበሉት ሁሉ ድነትንና ሕይወትን አስገኝቷል፡፡ በሌላ መንገድ ፈፅሞ ልናስተውል በማንችልበት መንገድ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ኃይል ገልጠውልናል፡፡ እጅግ አሰቃቂዎች ናቸው፣ ሆኖም ደግሞ ውቦች ናቸው፡፡ ለእግዚአብሔርም የማይለካ ክብርንና ምስጋናን ያመጡለታል፡፡ በአጭሩ፣ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከተከናወኑት ተግባራት ሁሉ ይልቅ እጅግ የከበሩ ናቸው፡፡

የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ሦስት ክፍሎች አሉት፣ በዮሐንስ 18፥1-19፥17 በሚገኘው ይጀምራል፡፡

*መያዝና በሸንጎ ፊት መቅረብ*

በመጀመሪያ በ18፥1-11 ውስጥ ኢየሱስ መያዙን እናነባለን፡፡ ይሁዳ ኢየሱስን ለአይሁድ ባለሥልጣናት አሳልፎ ከሰጠው በኋላ፣ ከሊቀ ካህናቱና ከፈሪሳውያን የተላኩ ወታደሮች መጥተው ኢየሱስን ያዙት፡፡ በ18፥12-27 ደግሞ፣ በሊቀ ካህኑ በቀያፋ ፊት ኢየሱስን ለጥያቄ አቀረቡት፡፡ በዚህ ወቅት፣ ልክ ኢየሱስ እንደተናገረው፣ ጴጥሮስ ኢየሱስን ሦስት ጊዜ ክዶታል፡፡

ቀጥሎም፣ በ18፥28-19፥16፣ ኢየሱስ በሮማው ገዢ በጲላጦስ ተፈትኗል፡፡ ጲላጦስ ኢየሱስ ምንም በደል የሌለበት መሆኑን ቢያረጋግጥም፣ አይሁድን ስለ ፈራ አልለቀቀውም፡፡ ከኢየሱስ መያዝና ለፍርድ መቅረብ ጀርባ ያለው እውነተኛ ኃይል ግን እግዚአብሔር ራሱ ነበር፡፡ ነገሩን የሚቆጣጠሩት ጲላጦስም ቀያፋም አልነበሩም፡፡ በዮሐንስ 19፥10-11 እንደምናነብበው፣ ሁሉ የተከናወነው እንደ እግዚአብሔር እቅድ ነበር፡፡

> ***ስለዚህ ጲላጦስ። አትነግረኝምን? ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? አለው።***
> ***ኢየሱስም መለሰ፡- ከላይ ካልተሰጠህ በቀር በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን ባልነበረህም፤ ስለዚህ ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ኃጢአቱ የባሰ ነው አለው።***
> ***(ዮሐንስ 19፥10-11)***

ስለ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ዮሐንስ ያቀረበው ዘገባ የሚገኘው ሁለተኛው ክፍል በዮሐንስ 19፥16-37 የሚገኘው ስቅላቱ ነው፡፡

**ስቅላት**

ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ሞት ባቀረበው ዘገባ፣ በስቅላቱ ወቅት የተከናወኑት ተግባራት ስለ መሲሁ በብሉይ ኪዳን የተነገሩ ተስፋዎችን መፈፀማቸውን ዮሐንስ አብራርቷል፡፡ እነዚህ ዝርዝሮች፣ ኢየሱስ በድንገት እንዳልተወሰደ፤ ሁሉም ነገር የተከናወነው እንደ እግዚአብሔር ዕቅድ መሆኑን ያሳያሉ፡፡

ኢየሱስ በመያዙ፣ ለፍርድ በመቅረቡና በስቅላቱ ወቅት፣ በፍፁም ፀጥታ የማይብረከረክ ክብሩን አሳይቷል፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ ነፍሱን ለህዝቡ አሳልፎ ሰጠ፣ ይህንንም በማድረጉ ከዚህ ቀደም

ተገልጦ በማያውቅ መንገድ የእግዚአብሔርን ክብር ገለጠ፡፡ እግዚአብሔር ህዝቡን ሊያድን ምን ያህል ርቀት ተጓዘ? ብትሉ፣ እስከ መስቀል ድረስ!

> **ኢየሱስ ከፊት ስለሚተብቀው ደስታ ሲል ወደ መስቀል እንደሄደ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ መስቀል ማንም ሰው በሕይወቱ ከሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ እጅግ የከፋው ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ የተቀበለውን መከራ ያህል የከፋ መከራ የለም፣ እርሱ ጭካኔ የሞላበትን አካላዊ ሞት ብቻ አልሞተም፣ ይልቁኑ የእኛን ኃጢአት ወስዶ፣ የእግዚአብሔርም ቁጣ በእርሱ ላይ አርፎበትም ሁሉን በጽናት ተሸከማቸው፡፡ ስለዚህ ነገሩ ማንም ሰው ሊያደርገው ከሚችለው በላይ የከፋ ነው፣ ኢየሱስ ግን በፊቱ ስላለው ደስታ ሲል አደረገው፡፡ ታዲያ እርሱ ያንን ለምን አደረገው? ያንን ያደረገው ውጤቱ ምን እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ክብር ያመጣል፡፡ ፍቅሩ፣ ፍትሁ፣ ቁጣው፣ ቅድስናው፣ ርኅራኄው እና ምህረቱ ሁሉም በአንድነት ውብ በሆነ መንገድ በመስቀል ላይ ተገለጡ፣ ከዚህም የተነሳ እኛም እርሱን በማንነቱ እናየዋለን ደግሞም በታረደው በግ ፊት ሆነን ለዘላለም እንድናመልከውም ያስችለናል፡፡ ዙፋኑ ባለበት እናመልከዋለን፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር በመስቀል ላይ ባህርዩንና ክብሩን አሳየን እኛም እናመልከዋለን፡፡ ብዙ ልጆቹንም በዚህ መስቀል ውስጥ ወደ ክብር አመጣቸው፡፡ እናም በመጨረሻ የሚመጣውን ፍሬ እያየ በደስታ አደረገው፡፡ (ዶ/ር ኬ. ኤሪክ ቶኔስ)**

ሦስተኛ፣ የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ዘገባ የሚያበቃው በዮሐንስ 20፥1-29 በሚገኘው በትንሣኤው በራሱ ነው፡፡

*ትንሣኤ*

ዮሐንስ 20፥1-9 እንደሚናገረው፣ የኢየሱስ ባዶ መቃብር ታሪካዊ እውነታ ነው፡፡ ማርያም፣ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ራሱ ኢየሱስ በዚያ እንዳልነበረ ዐይተዋል፡፡ በ20፥10-30 ውስጥ፣ ኢየሱስ ለመግደላዊት ማርያም፣ ለደቀመዛሙርቱ እና ለቶማስ ተገልጦላቸዋል፡፡ እነዚህ ዘገባዎች የሚያሳዩን የኢየሱስ ተከታዮች ዝም ብለው የሚነዱ ተላሎች ሳይሆኑ ተጠራጣሪዎች እነደነበሩ ነው፡፡

በተለይም፣ ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ለደቀመዛሙርቱ ሲገለጥ ቶማስ አልነበረም፡፡ ቶማስም ተጠራጣሪ ነበር፡፡ ማስረጃ ይፈልጋል፡፡ ስለ ትንሣኤ የሚነገር የእብዶች ታሪክ አያምንም፡፡ በቁጥር 27 ግን፣ ኢየሱስን በዐይኑ አየው፣ በቁጥር 28 የተመዘገበው የእርሱ ምስክርነት የዮሐንስ ወንጌል ትረካ የመጨረሻው እርከን ነው፡፡ ቶማስም "ጌታዬ አምላኬም" በማለት ለኢየሱስ እውቅና ሰጠ፡፡

> **ቶማስ በቅርብ ከሚያውቃቸው፣ እነዚህን ሁሉ ጊዜያት አብሯቸው ከኖረው፣ በውል ከሚያውቃቸው፣ ሰዎች ሰምቶ፣ ኢየሱስ ተነስቶ አየነው እያሉት፣ እንዲያው ዝም ሊቀበል አለመውደዱ በጣም አስገራሚ ነው፡፡ ባዕዳን ሰዎች አልነገሩትም ደግሞም ልዩነትም በመካከላቸው የለም፡፡ ሆኖም እርሱን ወደ እምነት አላመጣውም፡፡ እኔ እንደማስበው፣ እንደምጠረጥረውም ራሱን ለማመን ሰጥቶ እንደገና ማፈርን ያልወደደ ይመስላል፡፡ እንደገና ማዘንን ፈርቶታል ብዬ አስባለሁ፡፡ (ዶ/ር ዴቪድ ሬድሊንግስ)**

***ቶማስ “የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም” በማለት በጥርጣሬ የተናገራቸውን ቃላት እናውቃለን፣ ቶማስም “ተጠራጣሪው” የሚል ስም ወጥቶለታል፣ ምክንያቱም ኢየሱስን አላመነምና፣ እንደማስበው ግን ያን ያህል በቶማስ ባንጨክን ይሻላል፡፡ ኢየሱስ ራሱን ለዐሥራ ሁለቱ በገለጠበት በመጀመሪያው ወቅት፣ ቶማስ አለመኖሩን ዮሐንስ ይነግረናል፡፡ ሁለተኛ፣ ደቀመዛሙርቱ የኢየሱስ ትንሣኤ የዐይን ምስክሮች እንዲሆኑ መመረጣቸውን እስካመንን ድረስ፣ ቶማስ ያምን ዘንድ ሊያይ የሚገባው መሆኑን እናያለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ኢየሱስ በመካከላቸው ቆሞ ራሱን ለቶማስ ሲገልጥ፣ ከጠቅላላው ወንጌል እጅግ ድፍረት የተላበሰና ግልፅ የሆነን ምስክርነት ስለ ኢየሱስ ሰጥቷል፡፡ ኢየሱስን “ጌታዬ አምላኬም” በማለት ጠርቶታል፡፡ ስለዚህም ዮሐንስ በምዕራፍ 20፣ አንተ ስላየህ አምነሃል፣ ከዚህ በኋላ ግን ሳያዩ የሚምኑ የተባረኩ ናቸው፣ በማለት ኢየሱስ መናገሩን ዮሐንስ ገልጧል፡፡ ስለዚህ ያምን ዘንድ ቶማስ ማየጥ እንዳስፈለገው እናያለን፣ ግን እኛም ወደ ማየት እነደመጣንም እናስተውላለን፣ ያም ማለት ኢየሱስን በአካል በፊታችን ዐይተናል ማለት ሳይሆን፣ ስለ እኛ ሲሉ ያዩትን በማድነቅና በመረዳት ነው፡፡ ስለዚህ፣ አንዳንድ ጊዜ በቶማስ ላይ መጨከን አይገባንም ምክንያቱም ስርሱ ለየት ያለ ሚና ነበረውና ነው፡፡ ሚናውም አንድ ሰው ኢየሱስን ሲያይ፣ በአስደናቂ መንገድ በእርሱ ማመኑን የሚገልጥ የመሆኑ ተምሳሊት መሆን ነው፡፡ እንዲያውም እርሱ የሁላችን ተምሳሊት ነው፣ እኛ ሁላችን ኢየሱስን በማንነቱ ስንረዳው፣ በግንባራችን ተደፍተን እናመልከዋለን፡፡ (ዶ/ር ሲሞን ቫይበርት)***

የዮሐንስ ወንጌል የመጨረሻው ክፍል በዮሐንስ 211-25 የተመዘገበውና ስለ ኢየሱስ የምድር ሕይወትና አገልግሎት ያቀረበውን ዘገባ ያጠቃለለበት ክፍል ነው፡፡

# ማጠቃለያ

ይህ ማጠቃለያ በወንጌሉ በጠቅላላ የተቀመጡ መሪ ሃሳቦችን ነቅሶ ያወጣ እና አንባቢዎቹን ወደፊት የሚያመራ ነው፡፡ ቀደም እንዳለው ምዕራፍ ሁሉ፣ ከቁጥር 1-14 ድረስ ስለ ኢየሱስ የትንሣኤ መገለጥ ይዘግባል፡፡ የትረካው አፅንዖት ግን በመገለጡ እውነታ ላይ አልነበረም፡፡ በቁጥር 1 እና 14 በሁለቱም ይህንን መታየቱን መገለጥ ይለዋል፣ የተጠቀመውም ቃል በ2፥11 ውስጥ ኢየሱስ “ክብሩን ገለጠ” ብሎ በጠቀሰበት ዐይነት ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን መታየቱን የትንሣኤው ማረጋገጫ አድርገን ብቻ እንድናየው ሳይሆን በወንጌሉ በመጀመሪያው ምዕራፍ መገለጥ የጀመረው እና በዘገባዎቹ ሁሉ ቀጥሎ የነበረው ክብሩ ወደ ድምዳሜው የመጣ መሆኑን በመረዳት እንድናነብበው ዒላማ አድርጎ ነው፡፡

ከዚያም ባሻገር፣ ምንም እንኳን ቀዳሚው ሐዋርያ ጴጥሮስ ኢየሱስን ሦስት ጊዜ ቢክደውም፣ ሐዋርያቱና የተቀሩት ደቀመዛሙርት የኢየሱስ ምስክሮች ለመሆን ሥልጣን የተሰጣቸው መሆኑን ማጠቃለያው ያረጋግጥልናል፡፡ በዮሐንስ 2015-23 ውስጥ፣ የጴጥሮስን ክህደት ምህረት ለጴጥሮስ በማድረግ እና በሦስት ጥያቄዎች እርሱን በማደስ ቀልብሶታል፡፡ በእነዚህ ጎዳሴዎችም ጴጥሮስ

የእግዚአብሔርን መንጋ እንዲጠብቅ ኢየሱስ አደራ ሰጥቶታል፡፡ ኢየሱስ ራሱ መልካም እረኛ ነው፡፡ አሁን ግን የእግዚአብሔርን ህዝብ እንዲጠብቅ ጴጥሮስን ሾሞታል፡፡

ሌሎቹ ወንጌላት የሚያበቁት ታላቁን ተልዕኮ በተለያየ መንገድ በመግለፅ ነው፡፡ ያም ኢየሱስ ሐዋርያቱንና ሌሎቹን ደቀመዛሙርት ቤተክርስቲያንን እንዲመሠርቱ ያዘዘበት ነው፡፡ ይህ ስለ ጴጥሮ ኀዳሴ የሚናገረው ታሪክ ግን ስለ ቤተክርስቲያን የወደፊት ዮሐንስ ያለውን አተያይ የሚገልፅ ነው፡፡ ዘወትር ከህዝቡ ጋር እንደሚሆን ኢየሱስ ተስፋን ሰጥቷል፡፡ ከህዝቡ ጋር ዘወትር ከሚኖርባቸው መንገዶች አንዱም ጴጥሮስን የመሳሰሉ እረኞችን በመስጠት መሆኑን ለመግለፅ ይህንን ወቅት ተጠቅሞበታል፡፡ ጴጥሮስም በኋላ በ1ኛ ጴጥሮስ 5፥1-2 እንዲህ ጽፏል፡

> ***እንግዲህ እኔ፥ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ፥ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤***
> ***በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት፤ (1ኛ ጴጥ 5፥1-2)***

የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈው የመጨረሻዎቹ ሐዋርያት ሲሞቱ እንደሆነ አብዛኞቹ ምሁራን ያምናሉ፡፡ ምናልባትም በዚህ ወቅት በሕይወት ያለ የመጨረሻ ሐዋርያ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ስለዚህም፣ በመንጋው እረኞች አማካይነት ዛሬም ኢየሱስ አብሯቸው ያለ መሆኑን የእግዚአብሔር ህዝብ መስማቱ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ቤተክርስቲያንን የሚመራውም ጴጥሮስ ወይም ሌላ ሐዋርያ አልነበረም፡፡ የሚከተሉት ኢየሱስ ነበር፡፡ እነርሱ ያገለግሉ የነበረው እንደ እርሱ አምባሳደሮችና ረዳቶች ብቻ ነበር፡፡ ኢየሱስም ተመልሶ እንደሚመጣና፣ በአካልና ለዘላለም፣ እንደሚመራቸው ቃል ገብቷል፡፡

የዮሐንስን ወንጌል ዳራ፣ ውቅር እና ይዘት ከተመለከትን፣ ዮሐንስ አፅንዖት የሰጠባቸውን ጥቂት ዋና ርዕሶች እንመልከት፡፡

# 4. ዐቢይ መሪ ሃሳቦች

በዮሐንስ 2030-31 ዮሐንስ ዓላማውን ባሰፈረበት ቃል ውስጥ ወሳኝ የሆኑ መሪ ሃሳቦችን ዘርዝሯል፡፡ በዚያም እንዲህ ተጽፎ እናነባለን፡

> ***ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፤***
> ***ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል። (ዮሐ 20፥30-31)***

በትምህርታችን በዚህኛው ክፍል ውስጥ፣ ከዮሐንስ የዓላማ መግለጫ በወጡ አራት ተዛማጅ መሪ ሃሳቦች ላይ እናተኩራለን፡፡ እነርሱም፣ ማመን፣ የኢየሱስ ማንነት እንደ ክርስቶስ፣ ተዛማጅ ማንነቱ

እንደ እግዚአብሔር ልጅ እና የሚያስገኘው የሕይወት በረከት ናቸው፡፡ ኢየሱስ ስለ ማመን በሰጠው አፅንዖት እንጀምር፡፡

## *ማመን*

ዮሐንስ *pisteuo* የተሰኘውንና ትርጓሜው “ማመን” የሆነውን የግሪክ ቃል 106 ጊዜ ጠቅሶታል፡፡ ሦስቱ ወንጌላት በአንድነት የጠቀሱት 34 ጊዜ ብቻ ሲሆን፣ የዮሐንስ አንድ ሦስተኛ ብቻ ነው፡፡ ይህ የአፅንዖት ልዩነት በዮሐንስ ታሪክ ውስጥ ማመን የሚለው ሃሳብ ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ነው፡፡

በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ፣ ማመን የሚለው ሃሳብ “መቀበል፣” “መምጣት” እና “ማወቅ” በሚሉ ቃላት ከተገለጡ ሃሳቦች ጋር በብርቱ ይዛመዳል፡፡ ስለዚህ፣ በኢየሱስ ማመን ማለት እርሱን መቀበል፣ ወደ እርሱ መምጣት እና ግላዊ በሆነ ልምምድ እርሱን ማወቅ ማለት ነው፡፡

ይህን መሳዩ ማመን፣ መቀበል፣ ማወቅ እና ወደ ኢየሱስ መምጣት የሚጀምረው ኢየሱስን ለመከተል ባደረግነው የግል ውሳኔ ወቅት ነው፡፡ የዘመኑ ክርስቲያኖች ይህንኑ ተመሳሳይ ነገር “መለወጥ” ይሉታል፡፡ ለውጡ እውነተኛ ከሆነ፣ በእግዚአብሔር ሥራ ላይ እንድንሳተፍ፣ በተለያዩ መንገዶችም የእርሱን በረከቶች እንድንቀበል ያደርጉናል፡፡ በወንጌሉ በዚህ ክፍል ውስጥ፣ ዮሐንስ መለወጥ የሚለውን ቃል ያዛመደው የእግዚአብሔር ልጅ መሆን እና የዘላለምን ሕይወት ማግኘት ከሚሉት ቃላት ጋር ነው፡፡ በዮሐንስ 1፥12 ውስጥ ዮሐንስ ስለ ማመን የሰጠውን መግለጫ አድምጡ፡

> ***ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፡፡ (ዮሐንስ 1፥12)***

በዮሐንስ 3፥36 ውስጥም፣ እንዲህ የሚነበቡትን ተመሳሳይ ቃላት እናገኛለን፡

> ***በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም። (ዮሐንስ 3፥36)***

እነዚህን በመሳሰሉ ምንባቦች ውስጥ፣ ማመን እኛን ከእርሱ ጋር አንድ የሚያደርጉንን እውነተኛ፣ ከልብ የሆኑ እና ከእርሱም ጋር በግል የምንታመንበት እና ራሳችንን ለእርሱ የምንሰጥበትን ተግባር የያዘ ነው፡፡ እኛንም በታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ሥራ አካላት ያደርገናል፡፡ ወደ ሙላት የሚመጣውም ኢየሱስ በሙሉ ክብሩ በሚገለጥበት ወቅት ነው፡፡

እንግዲህ፣ ዮሐንስ “ማመን” የሚለውን ቃል ዘወትር በተመሳሳይ መንገድ እንደማይጠቀምበት መረዳት ይጠቅማል፡፡ በአንዳንድ ምንባቦች፣ “ማመን” የሚለውን ቃል ዮሐንስ የሚጠቀመው ውጫዊ የሆነውን እምነት ለማመልከት ነው፡፡ ይህንንም የነገረ-መለኮት ሊቃውንቱ “ጊዜያዊ” ወይም “የግብዝ” ብለው ይጠሩታል፡፡

ለምሳሌ፣ ዮሐንስ በ2፥23-24 ያቀረበውን ዘገባ አድምጡ፡

> *በፋሲካ በዓልም በኢየሩሳሌም ሳለ፥ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ ብዙ ሰዎች በስሙ አመኑ፤*
> *ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር፤ ስለ ሰውም ማንም ሊመሰክር ያስፈልገውም ነበርና አይተማመናቸውም ነበር፤ ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና። (ዮሐ 2፥23-24)*

ኢየሱስ በእነዚህ ሰዎች አይተማመንም ነበር ምክንያቱም እምነታቸው ውጫዊ ብቻ ስለነበር ነው፡፡ ይህም የነገረ-መለኮት ሊቃውንቱ "የሚያድን እምነት" እንደሚሉት አይነት እውነተኛ አይደለም፡፡

በአብዛኛዎቹ ክፍሎች፣ ዮሐንስ ስለ "ማመን" ሲናገር፣ ዘወትር በልቡ ያለው እውነተኛው የሚድነው እምነት፣ ማለትም ኢየሱስን አዳኝና ጌታ የማድረግ እውነተኛ መታመን እንደሆነ ከአውዱ መናገር እንችላለን፡፡ ለዮሐንስ፣ ልዩነቱ ያለው በኢየሱስ፣ በእምነታችን ባለቤት ነው፡፡ የሚያድነን የእምነታችን ኃይል ሳይሆን፣ ያመንነው የእርሱ ኃይል ነው፡፡

በኢየሱስ ማመን የተሰኘውን መሪ ሃሳብ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ እንድናምን ከሚፈልጋቸው መካከል፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ መሲሁ፣ ለህዝቡ ለእስራኤል እግዚአብሔር የሰጠው የቀድሞ ተስፋ ፍፃሜ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

# ክርስቶስ

ኢየሱስን "ክርስቶስ" ብሎ በመጥራት እርሱ የእስራኤል ንጉሥ መሆኑን ዮሐንስ በግልፅ አሳይቷል፡፡ እንዲያውም፣ "ክርስቶስ" ወይም "መሲህ" የተሰኘው ቃል በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን "የእስራኤል ንጉሥ" አቻ መጠሪያ ነበር፡፡ ክርስቶስ ማለት ይህ ነበር፡፡ ኢየሱስ እርሱ የእስራኤል ንጉ ነው የሚለው እውነታ በርካታ እንድምታዎች ነበሩት፣ ዮሐንስ ወደ ብዙዎቹ ትኩረትን ይስባል፡፡

ለምሳሌ፣ ልክ በብሉይ ኪዳን እንደነበሩት የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት፣ ኢየሱስ ለሚገዛቸው ሰዎች አርአያ በመሆኑ ላይ ዮሐንስ አጽንዖት ሰጥቷል፡፡ እስራኤል መሆን ከሚገባት በወረደችበት ሁሉ ኢየሱስ ሁሉን ሆኗል፣ በዚያም እስራኤል ሳታገኝ የቀረችውን በረከት ሁሉ ተቀብሏል፡፡ እንደ እስራኤል ንጉሥ፣ ኢየሱስ እስራኤልን በሁሉም አቅም ወክሏታል ደግሞም ምትካቸው እና የእግዚአብሔር በረከት መተላለፊያም ሆኗቸዋል፡፡

በዮሐንስ 15፥1-8 ውስጥ፣ ዮሐንስ ይህንን እውነት፣ ኢየሱስ እውነተኛ የወይን ግንድ፣ ተከታዮቹም የእርሱ ቅርንጫፎች መሆናቸውን በመዘገብ ገልፆታል፡፡

በዮሐንስ 15፥5-8 ኢየሱስ ምን እንደተናገረ አድምጡ፡

*እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ... በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል። ... ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከበራል። (ዮሐንስ 15፥5-8)*

በብሉይ ኪዳን በጠቅላላ፣ እስራኤል እንደ እግዚአብሔር የወይን ተክል ተገልጣለች፡፡ ይህንን ስዕላዊ መግለጫ መዝሙር 80፣ ኤርምያስ ምዕራፍ 2፣ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 17 እና ሆሴዕ ምዕራፍ 10 በመሳሰሉ ክፍሎች ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ በተጨማሪም፣ የዳዊት ንጉሣዊ ቤተሰብ እና ታላቁም መሲህ፣ የእግዚአብሔር ህዝብ እንደሚወጣባቸው ቅርንጫፎች ተገልጠዋል፡፡ ይህንንም በኢሳያስ 11፥1 ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ ስለዚህም፣ ይህንን ዳራ በማድረግ፣ ኢየሱስ እውነተኛ የወይን ግንድ እና እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘትና ማክበር የሚቻልበት ብቸኛ መንገድ ነኝ ሲል፣ ደቀመዛሙርቱ እርሱህዝቡን የሚወክልና አርአያ የሚሆን የእስራኤል እውነተኛ ንጉሥ መሆኑን ይረዳሉ፡፡

እንደ ንጉሥ፣ ኢየሱስ እርሱ እውነተኛው እስራኤል የመሆኑ ሃሳብ እንድምታዎች ምንድን ናቸው? አንዱ፣ እስራኤል ልትፈፅመው ተጠርታበት የነበረውን ነገር ኢየሱስ ፈፅሟል ማለት ነው፡፡ እስራኤል በእግዚአብሔር እንድትሆንና እንድታደርግ የተጠራችበትን ነገር ማድረግ ተስኗታል፡፡ እስራኤል በኃጢአት ምክንያት በወደቀችነት ሁሉ፣ ኢየሱስ በፍጹምነት አሳክቶታል፡፡ የእስራኤል የመሆኗንም ዓላማ ፈፅሞታል፡፡ በእርሱ ስብዕናም፣ የብሉይ ኪዳንን የዘመናት ታሪክ ኢየሱስ የደመደመ ሲሆን፣ እርሱ ብቻም ሊገልጥ የሚችለውን የእግዚአብሔር ክብር መገለጥ አሳይቷል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ የእስራኤል እውነተኛ ህዝብነት የእስራኤል ህዝብ አባል በመሆን ብቻ አይገለጥም፡፡ ይልቁኑ፣ የእውነተኛው ወይን ቅርንጫፍ የሆኑት፣ በኢየሱስ ያመኑትና ከእርሱም ጋር በእምነት አንድ የሆኑት ህዝብ ናቸው፡፡

ኢየሱስ እንደ ክርስቶስ በሚፈፅመው የውክልና ድርሻ ላይ የምናደርገው ውይይት የሚያተኩረው በሦስት መንገዶች ነው፡፡ ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ስለመሲሁ የተነገረው የተነገረውን ሁሉ የፈፀመ መሆኑ በተለይ ለዮሐንስ ወንጌል ወሳኝ ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ መቅደሱ የተነገረውን ፈፀመ፡፡ ሁለተኛ፣ ከእስራኤል በዓላት ይጠበቅ የነበረውን ፈፅሟል፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ የእግዚአብሔርን ህግ ፈፅሟል፡፡ ስለ መቅደሱ የተነገረውን በመፈፀሙ እንጀምርና ሁሉንም በየተራ እንመለከታቸዋለን፡፡

## መቅደስ

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መቅደሱ ወሳኝ የሆነበት አንዱ ምክንያት፣ እግዚአብሔር ለየት ባለ መንገድ በህዝቡ መካከል እንደሚገኝ ተስፋን የሰጠበት ስፍራ በመሆኑ ነው፡፡ እርግጥ ነው፣ እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ የሚገኝ መሆኑን እናውቃለን፤ እርሱ በሁሉም ስፍራ ሁል ጊዜ ይገኛል፡፡ ስለ እርሱ ልዩ መገኘት ስንናገር ግን፣ የመገኘቱን መገለጥ በልቡናችን ይዘን ነው፡፡ ይህም በገሃድ በሚታይ ክብር በተወሰነ ስፍራ ህልውናውን እንዲታወቅ የማድረጉን እውነታ ያሳያል፡፡

**በመገናኛው ድንኳን እና በመቅደሱ ውስጥ የእግዚአብሔር መገኘት ወሳኝ ነው ምክንያቱም የመገናኛው ድንኳንና መቅደሱ ፍጥረተ-ዓለም በትንሹ ማለት ናቸው፡፡ እነርሱ ዓለም በትንሹ ማለት ሲሆኑ፣ የእግዚአብሔር በዚያ መገኘትም የእርሱን በዓለም ላይ መገኘት የሚወክል ነው፡፡ ዓለም እርሱ ከህዝቡ ጋር ግንኙነት የሚያደርግባት**

**መቅደስ ናት፡፡ ከዚያም፣ አዳም ሲያምፅ፣ እግዚአብሔር አንድ ወገን መረጠ ያም በመጨረሻው እስራኤል ሆነች፣ በመካከልዋም መኖሪያን አደረገ፣ በመካከላቸው የሚገኘውም በዚያ የፍጥረተ-ዓለሙ ትንሽ መገለጫ በሆነው ስፍራ ነበር፡፡ በዚያ መገኘቱም ልዩ ነበር ምክንያቱም እስራኤል በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ለመሆን ወደዚያ፣ ማለትም ወደ መገናኛው ድንኳን፣ በመቅደሱ ወደሚገኘው መሰዊያ ትሄድ ነበርና ነው፡፡ ይህም ወደፊት እግዚአብሔር በመላው ዓለም የሚያደርገው ነገር ቅምሻ ነው፡፡ የመገናኛው ድንኳን በዘፀአት ማብቂያ ላይ ሲጠናቀቅና ሲመረቅ እግዚአብሔር የመገናኛውን ድንኳን ሲሞላው እና በኋላም በ1ኛ ነገሥት 8 መቅደሱን ሲሞላው፣ በመላው ዓለም የእግዚአብሔር ክብር በሙላት ሲገለጥ ምን እንደሚሆን ናሙናውን እንድናየው አድርጎናል፡፡ (ዶ/ር ጀምስ ሃሚልተን)**

በህዝቡ መካከል የእግዚአብሔር ልዩ መገኘት በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች ተገልጧል፡፡ በመጀመሪያ፣ ኤደን ገነት የእግዚአብሔር ልዩ መገኘት ያለባት በምድር የተቀደሰች ስፍራ ናት፡፡ የምታገለግለውም በምድር እንዳለ የዙፋኑ ማረፊያ ነበር፣ ከዚያም የሰው ዘር ዓለምን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር የተቀደሰ መንግሥት በመለወጥ መላውን ዓለም ይቀድሳል፡፡

በኋላም፣ እስራኤልን የመንግሥቱ ካህን አድርጎ ሲመሠርታት፣ የእርሱን መገኘት በመጀመሪያ ከመገናኛው ድንኳን ኋላ ደግሞ ከመቅደሱ ጋር እንዲያያዝ አደረገ፡፡ የመቅደሱ ማስዋቢና የመገልገያ እቃዎች ሁሉ የኤድን ገነትን ተምሳሊት የያዙ ነበሩ፡፡ የመገናኛውም ድንኳን ሆነ መቅደሱ ያገለግሉ የነበሩት እንደ ገነቷ ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍትም ይህንን ትስስር የገለጡት የመገናኛው ድንኳንና መቅደሱ የእግዚአብሔር ንጉሣዊ ዙፋን በምድር ማለትም በህዝቡ መካከል በክብር የሚያድርበትን ስፍራ በማመልከት ነው፡፡ ይህ እውነታ በ1ኛ ዜና 28፥2፣ በመዝሙር 11፥4 እና በኢሳያስ 6፥1 በግልፅ ተቀምጧል፡፡ እነዚህም በመላው ዓለም እጅግ የተቀደሱ ስፍራዎች ናቸው፡፡ በእነዚያም ስፍራዎች የእግዚአብሔርን በረከቶች ህዝቡ ተዘጋጅተው የሚያገኙባቸው ናቸው፡፡ ልክ እንደ ኤድን ገነት፣ የመንግሥቱ ማዕከላት ነበሩ፣ ህዝቡም ዓለምን እንደ መንግሥቱ ዓለምን በእነዚያ ይቀድሳል፡፡ እንደ ዮሐንስ ወንጌል አገላለፅም፣ የኢሱስን አስፈላጊነት የምንረዳበት ወሳኝ መንገድ በብሉይ ኪዳን የተነገሩ የመገናኛውን ድንኳንና የመቅደሱን ተስፋዎች የፈፀመ መሆኑን በማየት ነው፡፡ በዮሐንስ 1፥14 ዮሐንስ የጻፈውን አድምጡ፡

***ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን። (ዮሐ፯ስ 1፥14)***

ዮሐንስ “በእኛ አደረ” በማለት ስለ ኢየሱስ ሲናገር፣ የተጠቀመው *skenoō* የተሰኘውን የግሪክ ቃል ሲሆን የሚዛመደውም *skēnē*, ከሚለው ስም ጋር ሲሆን ትርጓሜውም ድንኳን ወይም መገናኛ ማለት ነው፡፡ እንዲያውም፣ ይኸው ተመሳሳይ ስም በሰብዓ ሊቃናት (ግሪክኛ የብሉይ ኪዳን ቅጂ) ውስጥ የእግዚአብሔርን ቅዱስ መገናኛ ለመግለጥ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ይህንን ግሥ በመጠቀምና በእግዚአብሔር መገኘት ከሚገለጠው ክብር ጋር በማገናኘት፣ ከዚህ ቀደም በመገናኛው ድንኳን ይገኝ ወደ ነበረው የእግዚአብሔር ልዩ መገኘት እንደምንገባ ዐይነት ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር የምንገባበትን በር መክፈቱን ዮሐንስ ግልፅ አድርጎታል፡፡

በዮሐንስ 2፡19-21 ውስጥ ዮሐንስ ስለ መቅደሱ ተመሳሳይ የሆነ ሃሳብ አስፍሯል፣ እንዲህ ይነበባል፡

> *ኢየሱስም መልሶ፦ ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፥ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው።*
>
> *ስለዚህ አይሁድ። ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር፥ አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት።*
>
> *እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር። (ዮሐ 2፥19-21)*

በዚህ ስፍራ፣ ኢየሱስ ስለ መቅደሱ የተነገረውንም እንደፈፀመ ዮሐንስ ግልፅ አድርጎታል፡፡

ኢየሱስ ከዚያ በኋላ በምድር በአካል ባይመላለስም፣ ተከታዮቹ ግን በእግዚአብሔር ልዩ መገኘት ደስታ ውስጥ እንደሚሆኑም ዮሐንስ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ በዮሐንስ 4፥21 ውስጥ፣ እግዚአብሔርን ለማምለክ የአይሁድ መቅደስም ሆነ የሳምራውያን የተቀደሰ ስፍራ ልዩ ግምት የማያገኙበት ጊዜ በቶሎ እንደሚመጣ ኢየሱስ ለሳምራዊቲቱ የነገራት ለዚህ ነው፡፡ ኢየሱስ በዮሐንስ 4፥23-24 ውስጥ እንዲህ ብሏል፡

> *ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ … እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል። (ዮሐ 4፥23-24)*

ኢየሱስ ለሳምራዊቲቱ ሴት የነገራት ቃል ለዘመናችን ቤተክርስቲያን ትልቅ ማበረታቻ ነው፣ ምክንያቱም እኛ የምንኖረው ኢየሱስ በተናገረለት ወቅት ላይ ነውና፡፡ በእኛ ዘመን፣ ኢየሱስ በአካል በምድር የለም፡፡ ዕብራውያን 8፥2 እና 9፥11-12 እንደሚናገሩት፣ እርሱ በአካል የሚኖረው በሰማይ ባለው በእግዚአብሔር መቅደስ ነው፡፡ በመንፈስ ግን ከእኛ ጋር አለ፣ በተለይም እንደ ቤተክርስቲያን በአንድነት ስንሆን፡፡ ይህንንም በማቴዎስ 18፥20 እና በ1ኛ ጴጥሮስ 2፥4-9 ውስጥ እናየዋለን፡፡ ኢየሱስ ከእኛ ጋር በመሆኑ ምክንያት፣ እኛ በምድር እግዚአብሔር የሚኖርበት የተቀደሰ መቅደሱ ነን፡፡

ይህ በክርስቶስ የተፈፀመው አስደናቂ የመቅደሱ ሙላት ኢየሱስ በክብር ሲመለስ የላቀ ይሆናል፡፡ ራእይ 21፥1-5 የመሳሰሉት ስፍራዎች እንደሚያስተምሩን ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ፣ ፍጥረተ ዓለሙን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መገኛነት ይለውጠዋል፡፡ በዚያን ወቅት፣ ክርስቶስና አብ ከእኛ ጋር ለዘላለም ይኖራሉ፣ ምድርም በእግዚአብሔር ክብር ትሞላለች፡፡

በዮሐንስ ወንጌል ኢየሱስ የፈፀመው ብሉይ ኪዳናዊ ተስፋ ሁለተኛው መንገድ የእስራኤልን በዓላት ፋይዳ ወደ ሙላት ማምጣቱ ነው፡፡

**በዓላት**

ቀደም ብለን እንደጠቀስነው፣ አብዛኛው የዮሐንስ ወንጌል የተዋቀረው ኢየሱስ በተካፈለባቸው የተለያዩ በዓላት ዙሪያ ነው፡፡ ከእነዚህም በዓላት መሃል የፋሲካ፣ የዳስ እና የቤተ መቅደሱ መታደስ ይጠቀሳሉ፡፡ እግዚአብሔር እነዚህን በዓላት የደነገገው እስራኤልን የእርሱ የካህናት መንግሥት ለማድረግ እና በመገናኛው ድንኳንና በመቅደስ ውስጥ የእርሱን በረከት የሚቀበሉበትን መደበኛ

መስመር ለመዘርጋት ነው፡፡ ዮሐንስም በወንጌሉ፣ የእነዚህን በዓላት ፋይዳ ኢየሱስ መፈፀሙን ግልፅ አድርጓል፡፡

የፋሲካ በዓል ከእስራኤል ዐበይት ሦስት ዓመታዊ ክብረ በዓላት አንዱ ነው፡፡ የእስራኤል ከግብፅ መውጣት ይከበርበታል፡፡ በአጭሩ፣ ኢየሱስ ይህንን በዓል ፈፅሞታል ምክንያቱም እርሱ በፋሲካ እንደታረደውና እንደተበላው፣ ደሙም የእስራኤል ከግብፅ ባርነት ነፃ የመውጣት ምልክት የሆነው የፋሲካ በግ ተምሳሊት ነውና፡፡ አራቱም የወንጌላት ጸሐፍት ኢየሱስን እውነተኛው የፋሲካ በግ ብለውታል፡፡ ዮሐንስ ብቻ “እነሆ፣ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!” የሚለውን የመጥምቁ ዮሐንስን ቃል፣ በዮሐንስ 1፥29 በመጥቀስ ይህንን እውነታ አስምሮበታል፡፡ በዮሐንስ 19፥33 ውስጥ፣ ኢየሱስ ሲሞት፣ ወታደሮቹ “ጭኑን አልሰበሩም” የሚለውን በመዘገብ፣ በዘፀአት 12፥46 ለፋሲካ በዓል የሚመረጠው በግ ጭን እንዳይሰበር የተሰጠው ትዕዛዝ ፍፃሜ ሆኗል ይለናል፡፡ በእነዚህና በሌሎችም መንገዶች፣ ኢየሱስ የፋሲካን ተምሳሊትነትና ፋይዳ ፈፅሟል በማለት ዮሐንስ ያሳየናል፡፡

በዮሐንስ 7፥2፣37 ውስጥ፣ ኢየሱስ ሌሎች ሦስት የእስራኤልን ዓመታዊ በዓላት ዮሐንስ ዘግቧል፡፡ እነርሱም፡ የዳስ በዓል፡፡ በዚህ በዓል ከሚከናወኑት ሥርዓቶች አንዱ እግዚአብሔር ለእስራኤል በምድረ በዳ ውሃን መስጠቱን፣ ከዚያም ከዓመት እስከ ዓመት የመኸር ዝናብ ማዝነቡን፣ በመጨረሻውም ቀን እግዚአብሔር የበረከትን ምንጮች በህዝቡ ላይ የሚያፈስስ መሆኑን የሚያመለክተው ውሃ የማፍሰሱ ሥርዓት ነው፡፡ ዮሐንስም በዚህ ክብረ በዓልና በኢየሱስ መካከል ጠንካራ ግንኙነት በመመሥረት በታሪክ ፍፃሜ ኢየሱስ የእግዚአብሔር በረከቶች ሁሉ መገኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በተለይም፣ በዳስ በዓል የመጨረሻ ቀን፣ የእግዚአብሔርን በረከት ያፈስስ ዘንድ ኢየሱስ ኃይሉን ማወጁን ዮሐንስ ዘግቧል፡፡ ኢየሱስ በዮሐንስ 7፥37 ውስጥ ለህዝቡ የተናገረውን አድምጡ፡

> ***ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። (ዮሐ 7፥37)***

የእግዚአብሔር በረከት የሆነው የሕይወት ውሃ የሚመነጨው ከኢየሱስ መሆኑን ዮሐንስ ዘግቧል፡፡ ያለፈው፣ የአሁኑና የሚመጣው በረከት ሁሉ የሚገኙት በእርሱ ነው፡፡ በዚህ መንገድ፣ በዳስ በዓል ውስጥ በግልፅ የተቀመጡት የእግዚአብሔር የበረከት ተስፋዎች ፍፃሜ ኢየሱስ ነው ማለት ነው፡፡

በመጨረሻም፣ በዮሐንስ 10፥22-39 ውስጥ፣ ኢየሱስ የቤተመቅደሱን የመታደስ በዓል ወይም ሃኑካን አክብሯል፡፡ የቤተመቅደሱ የመታደስ በዓል በብሉይ ኪዳን ከነበሩ ታላላቅ በዓላት አንዱ አልነበረም፡፡ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የእስራኤል ታሪክ ውስጥ ግን ጉልህ ስፍራ ነበረው፡፡ ምክንያቱም እስራኤል በ165ዓ.ዓ. በግሪክ ላይ የተቀዳጀችው ድል፣ ደግሞም ከድሉ በኋላ መሰዊያውና መቅደሱ እንደገና የታደሱበት በዓል የሚከበርበት ነበርና ነው፡፡ በዮሐንስ 10፥30 ውስጥ፣ የቤተመቅደሱን የመታደስ በዓል ካከበረ በኋላ፣ ኢየሱስ የሚከተለውን አስደንጋጭ እውነታ ተናግሯል፡፡

> ***እኔና አብ አንድ ነን። (ዮሐንስ 10፥30)***

አይሁድም አምላክ ነኝ ማለቱን ስለተረዱ፣ በድንጋይ ይወግሩት ዘንድ ተነሱ፡፡ ኢየሱስም በዮሐንስ ፲፥36 የጠቀሰውን ሙግት በማቅረብ ተከላከለ፡፡

*... አብ የቀደሰውን ወደ ዓለምም የላከውን። (ዮሐ ፲፥36)*

እርሱ "የተላከ" መሆኑን ኢየሱስ ሲናገር ፣ የተጠቀመው መደበኛውን የግሪክ ቃል *hagiazō ነው፣* ቅዱሳት መጻሕፍት በቤተመቅደስ ውስጥ በሚከናወኑ *ሥርዓቶች* የሚካሄደውን የመቀደስና የመለየት *ሥርዓት* ለማመልከት ይጠቀሙበታል፡፡ በዚህ አውድ፣ *hagiazō የሚለው ቃል* *egkainia* ከተሰኘው እና "መታደስ" ከተሰኛውና "የመታደስ በዓል" መግለጫ ከሆነው የግሪክ ቃል ጋር ቅርበት አለው፡፡

በነዚህ መንገዶች፣ ዮሐንስ ኢየሱስን ከመቅደሱ የመታደስ ወይም የመቀደስ በዓል ጋር በቅርብ አስተሳስሮታል፡፡ በዓሉ የሚከበረው መቅደሱ ለእግዚአብሔር መገኘት መለየቱን ለማመልከት ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድም፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልዩ መገኘት በምድር ፍፃሜ ይሆን ዘንድ ተልኳል፡፡

ኢየሱስ ስለ መቅደሱ የተነገረውና የበዓላቱ ፍፃሜ መሆኑን ከማሳየቱ በተጨማሪ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔርንም ህግ መፈፀሙን ዮሐንስ አሳይቷል፡፡

### *ህግ*

ምንም እንኳን ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ህግ በአሉታዊ መንገድ የመመልከት ማለትም የሚኮንነን እንደሆነ የመቁጠር ልማድ ቢኖራቸውም፣ ህጉ ግን ወደ እግዚአብሔር በረከት የሚወስድ መምሪያ ሆኖ ለእውነተኛ አማኞች እንደተሰጠ ማስታወስ ይገባል፡፡

> **በመጽሐፍ ቅዱስ የተቀመጠውን ህግ በምትመለከቱበት ወቅት፣ የሚያነብቡት ሰዎች የደንብና የመመሪያ ዝርዝሮችን እንደሚያነቡ ዓይነት ሊያምኑ አይገባም፡፡ ይልቁኑ የሕይወት መመሪያ ነው፡፡ ሊያነብቡት የሚገባውም ያንን በማወቅ ነው፣ ህጉን ቢጠብቁ፣ በመጠበቃቸው ይባረካሉ፣ ለዚያም በርካታ ምክንያት እንዳለ አስባለሁ፡፡ አንዱ ህጉ የእግዚአብሔር መገለጥ በመሆኑ ነው፡፡ እግዚአብሔር እንዴት እንድንኖር እንደሚፈልግ ህጉ ይነግረናል፡፡ መዝሙረኛውም በ40 ቁጥር 8 ላይ፣ "አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ፥" ይላል፡፡ ራሳችንን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ስናስማማ፣ የእግዚአብሔርም ፈቃድ ምን እንደሆነ ስንረዳ፣ ልናደርግ የሚገባንን በማድረግ እና ልናደርግ የማይገባንን ባለማድረግ ታላቅ ደስታና በረከት እንቀበላለን፡፡ ስለዚህም የእርሱ መገለጥ የእግዚአብሔር በረከት፣ እና የእግዚአብሔር ሞገስ ምልክት ነው፡፡ ከዚያ ባሻገር እንደማስበው ግን፣ ህጉ እግዚአብሔር በዚህ ምድር ሊያመጣ ባለው ነገር ውስጥ ተሳታፊ እንሆን ዘንድ ግብዣን የተቀበልንበት በረከት ነው፡፡** (ዶ/ር ስቲቭ ሃርፐር)
>
> **በብሉይ ኪዳን የህጉ አጠቃቀም አዎንታዊነቱ የጎላ ነው ምክንያቱም የእግዚአብሔር ህግ የእግዚአብሔር ባህርይ መገለጫ ነውና፡፡ እናም መዝሙራት፣ ለምሳሌ የእግዚአብሔር**

*ህግ ለእግራችን መብራት ለመንገዳችንም ብርሃን መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ዳዊትም መበዝሙሩ ከማር ወለላ እንደሚጣፍጥ፣ ከከበረ ዕንቁ እንደሚልቅ፣ ባሪያውም በመጠበቁ እንደሚታረም እና ታላቅ ብድራት እንዳለበትም ይናገራል፡፡ በመሠረቱ፣ መዝሙረ ዳዊት የሚጀምረው ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፥ በማለት ነው፡፡ ከዚያም መዝሙር 1 እግዚአብሔርን የሚፈራና ህጉንም የሚጠብቅ ሰው በወንዝ ዳር እንደተተከለና ፍሬውም እንደማይቋረጥ ዛፍ የመሆኑን ምስል ያስቀምጣል፡፡ ስለዚህ ህጉ የመባረክ ስፍራ ነው፡፡ ሆኖም የመባረክ ስፍራ የሚሆንላቸው በክርስቶስ በኩል የሚገኘውን ይቅርታ ከእግዚአብሔር ለተቀበሉ ብቻ ነው፡፡ ግን ህጉ በክርስቶስ የሚገኘውን ሕይወት የበረከት ሕይወት እንዴት ልናደርገው እንደምንችል የሚመራን መምሪያ ነው፡፡ ጳውሎስ እንደሚናገረው፣ የህጉ ግብ ወይም ዓላማ ነው፣ ስለዚህ ክርስቶስን የሚወድድ ህጉን ይፈፅማል፡፡ ህጉ ስለ ኃጢአት ያስተምረናል፣ ኢየሱስ ለእኛ ምን እንዳደረገልንም ያሳየናል ከዚያም መኖር የምንችልበትን ምሪትም ይሰጠናል፡፡ ኢየሱስ እንደተናገረው፣ ሕግ ሁሉ በሁለቱ ትዕዛዛት ተጠቃሏል፡ እግዚአብሔርን በፍፁም ልብ፣ ነፍስ፣ አዕምሮና ኃይል ሁሉ መውደድ፣ ባልንጀራን እንደራስ መውደድ፡፡ እግዚአብሔርን በፍፁም ልቡ፣ ነፍሱ፣ አእምሮውና ኃይሉ የሚወድድን ሰው ካወቃችሁ፣ ያ ሰው የሚጠብቀውን በረከት ታውቃላችሁ፡፡ ባልንጀራውን እንደ ራሱ የሚወድድንም ሰው ካወቃችሁ የዚያ ሰው በረከት ምን ያህል ታላቅ እንደሚሆን ታውቃላችሁ፡፡ ለእግዚአብሔር ህግጋት በታማኝነት በቆሙ ሰዎች ዙሪያ ከተገኛችሁ፣ በዚያ ቸርነት፣ ምህረት፣ መግቦት እና ባርኮት አለ፡፡ (ቄስ ሚካኤል ጉሎዶ)*

በብሉይ ኪዳን፣ የእግዚአብሔር ህግ ለህዝቡ እንደተሰጠ ልዩ ስጦታ ነው፡፡ መዝሙር 119 እና ሌሎችም በርካታ ምንባቦች ወደ እግዚአብሔር በረከት እስራኤልን የሚመራ ብለው አወድሰውታል፡፡ በአዲስ ኪዳን ደግሞ፣ በያዕቆብ 1፥25 ውስጥ የእግዚአብሔር ህግ ነፃነትን የሚሰጥ ፍፁም ህግ ተብሏል፡፡ ጳውሎስ ደግሞ በ1ኛ ቆሮንቶስ 9፥21 ውስጥ፣ የክርስቶስ ህግ ብሎታል፡፡ ኢየሱስም የህጉን አስፈላጊነት በዮሐንስ 10፥35 ውስጥ እንዲህ አስቀምጦታል፡

*መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና ... (ዮሐ 10፥35)*

በዚህ ስፍራ ኢየሱስ፣ ብሉይ ኪዳን በጠቅላላ፣ ህጉንም ጨምሮ፣ በህዝቡ መካከል ያለማቋረጥ የሚኖር ቃል ነው በማለት አስተምሯል፡፡

ሆኖም፣ ህጉ በራሱ የመደምደሚያ እንዳልሆነ ዮሐንስ ግልፅ አድርጎታል፡፡ ትርጉም በሚሰጥ መንገድ፣ ዘወትር ከራሱ አሻግሮ ወደ ክርስቶስ ያመለክታል፡፡ በዮሐንስ 5፥46-47 ውስጥ ለማያምኑት አይሁድ እንዲህ ብሏል፡

*ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር፤ እርሱ ስለ እኔ ጽፎአልና። መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ? (ዮሐ 5፥46-47)*

ዮሐንስ ይህንን ነጥብ በወንጌሉ በጠቅላላ ነካክቶታል፡፡ የብሉይ ኪዳን ህግ ወደ ኢየሱስ ያመለክታል፡፡ ስለዚህ፣ ኢየሱስን አለመቀበል ማለት አስቀድሞ ስለ እርሱ የተናገረውንም አለመቀበል ነው፡፡

ዮሐንስ ይህንን ነገር አፅንዖት የሰጠበት አንዱ መንገድ ይሁዲነት ቀድሞውኑ ለህጉ ሰጥቷቸው የነበረውን መጠሪያ፣ ባህርያት እና ተግባራት ለኢየሱስ መስጠት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ይሁዲነት የተራበውን ጠላትህን "የቶራን እንጀራ መግብ" ይላል፡፡ በዮሐንስ 6፥35 ኢየሱስ "የሕይወት እንጀራ" ተብሏል፡፡ ይሁዲነት "የቶራ ቃሎች ለዓለም ሕይወት ናቸው" ይላል፡፡ በዮሐንስ 4፥11፣ ኢየሱስ የሕይወትን ውሃ የሚሰጥ ተብሏል፡፡ ይሁዲነት በተጨማሪም "ለሰው ሁሉ ያበራ ይሆን ዘንድ የተሰጠ የህግ ብርሃን" ይላል፡፡ ዮሐንስ 1፥9 ደግሞ፣ ኢየሱስን "ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛ ብርሃን" ይለዋል፡፡ እነዚህ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ህጉ በአካል እንደገለጠው የሚያሳዩ በዮሐንስ ወንጌል ከተጠቀሱት ከብዙ በጥቂቱ ናቸው፡፡ ኢየሱስ እና ትምህርቶቹ ለሚከተሉት ሁሉ የሕይወትና የብርሃን ምንጭ እንደሆኑ ይቀጥላሉ፡፡

ለኢየሱስ ክርስቶስ መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ አንባቢዎቹ እንዲረዱ ዮሐንስ ይናፍቃል፡፡ ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን እንደማይተው እና ዘወትርም ከእኛ ጋር እንደሚሆን በማወቅ እንዲጽናኑ ይፈልጋል፡፡ ኢየሱስን በማመን፣ በእርሱ አማካይነት የእግዚአብሔርን በረከት እንዲቀበሉ ይፈልጋል፡ ለእግዚአብሔር ቃልም ታዛዦች እንዲሆኑና እንደ መንግሥቱ ካህናት ጌታን እንዲያከብሩም ይፈልጋል፡፡

በኢየሱስ ማመን እና የኢየሱስ ማንነት እንደ ክርስቶስ የተሰኙትን መሪ ሃሳቦች ከተመለከትን፣ ተዛማጅ የሆነውን እንደ እግዚአብሔር ልጅ ያለውን ማንነቱን ደግሞ እንመለከታለን፡፡

## የእግዚአብሔር ልጅ

እንደ እግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ማንነት ከክርስቶስነቱ ጋር ተዛማጅ ነው ምክንያቱም ሁለቱም የሚያመለክቱት እርሱ በምድር ያለችው የእግዚአብሔር መንግሥት ንጉሥ መሆኑን ነው፡፡ እንዳንዳቸው በቀላ የማይታይ ገፅታ ስላላቸው እነዚህን አባባሎች ለየብቻ መመልከታችን አስፈላጊ ነው፡፡

በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የእግዚአብሔር ልጅ የሚለው አባባል መለኮታዊውን መሲሃዊ ንጉሥ ያመለክታል፡፡ በአንድ በኩል፣ በዮሐንስ 10፥22-40 ውስጥ፣ ከሰማያት ወደ ምድር የመጣውን የመለኮታዊ ወልድ ፅንሰ ሃሳብ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ በዮሐንስ 1፥49 እና 11፥27 እንደምናየው፣ ከእስራኤል ንጉሥ ወይም ከክርስቶስ፣ ከዳዊት ዘር የሆነውንና የተገባውን የእስራኤል ንጉሥነቱን ያመለክታል፡፡

በዮሐንስ ወንጌል ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ማለት ምን ማለት እንደሆነ በበለጠ ለመረዳት፣ ኢየሱስ ፍፁም መለኮት ፍፁምም ሰው ነው የሚለውን መረዳት ያስፈልገናል፡፡ ምክንያቱም በውስጡ ያለውን ምሥጢር እንድናይ ያደርገናል፡፡ በመጀመሪያ ኢየሱስ ፍፁም መለኮት ነው የሚለውን እንመልከት፡፡

## መለኮት

ዮሐንስ የወልድን መለኮትነት ከገለጠባቸው መንገዶች አንዱ በወልድ በኢየሱስና በእግዚአብሔር አብ መካከል ያለው ግንኙነት ነው፡፡ ይህ ግንኙነት ከሰው ዘር ጋር፣ ማለትም ከአማኞች ጋር ካለው ግንኙነት እጅግ የላቀ መሆኑን የሚያሳዩ በርካታ ምንባቦች አሉ፡፡

በዮሐንስ 10፥30-33 በኢየሱስና በአይሁድ መካከል የተደረጉ ንግግሮችን አድምጡ፡

> ***እኔና አብ አንድ ነን።***
> ***አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ።***
> ***ኢየሱስ፦ ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ፤ ከእነርሱ ስለ ማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ? ብሎ መለሰላቸው።***
> ***አይሁድም። ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት። (ዮሐ 10፥30-33)***

ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ባለው ግንኙነት አንድ መሆናቸውን ሲያውጅ፣ አምላክ ነኝ እያለ ማወጁ እንደሆነ አይሁድ በትክክል ተረድተዋል፡፡

ከዚያም ባሻገር፣ ዮሐንስ 14፥9 እንደሚናገረው፣ ማንም ሊያደርገው በማይችለው ዓይነት ኢየሱስ እግዚአብሔር አብን የገለጠ ልዩ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፡፡ ዮሐ 1፥18 “ልጅ” የሚለውን ቃል ባይጠቀምም አሳቡ ግን አንድ ነው፡፡ ኢየሱስ አባቱን ለህዝቡ በትክክል ገልጿል፡፡ እንዲያውም፣ በዮሐንስ 14፥9 ኢየሱስ እንደተናገረው፣ ኢየሱስን ማየት ማለት አብን ማየት ማለት ነው፡፡

ከነዚህ መገለጦች ባሻገር፣ ኢየሱስ በሕይወት፣ በሞት እና በመጨረሻው ፍርድ ኢየሱስ ሙሉ መለኮታዊ ሥልጣን አለው፡፡ ይህም በዮሐንስ 5፥21-22 እንዲህ ይነበባል፡፡

> ***አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው፥ እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል። ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። (ዮሐ5፥21-22)***

ኢየሱስ ስጋ የሆነው አምላክ መሆኑን ዮሐንስ ግልፅ አድርጓል፡፡ የእግዚአብሔርን ሥራ በምድር ይፈፅም ዘንድ ያልተገደበ ሥልጣን የነበረው፣ አምላክ ነበር፡፡

ዮሐንስ የኢየሱስን መለኮትነት ወይም አምላክነት የገለፀበት ሌላው መንገድ ኢየሱስ እኔ ነኝ ያለበትን መግለጫ መጠቀም ነው፡፡ በዘፀአት 3፥14፣ እግዚአብሔር ለሙሴ የቃል ኪዳን ስሙን "**እኔ እኔ ነኝ**" በማለት ገልፆለታል፡፡ ይህም በአማርኛው ቅጂ "ጌታ" ተብሎ የሚገለጠው መለኮታዊ ስም መሠረት ነው፡፡ በኢየሱስ ዘመን በአይሁዳውያን ዘንድ የእግዚአብሔር ስም ቅዱስ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ስሙ መጠራቱን ይቃወማሉ፡፡ ኢየሱስ ግን ለራሱ ተጠቀመበት፡፡

> **በዮሐንስ ወንጌል፣ "እኔ ነኝ" የሚለው ዐረፍተ-ነገር በኢየሱስ ንግግሮች ውስጥ 24 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ ከሌሎቹ ወንጌላት ይበልጥ የተጠቀመበት ሲሆን፣ ከአጠቃላዩ አዲስ ኪዳን ደግሞ ገሚሱ ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ያለው ወሳኝነት ኢየሱስን ከብሉይ ኪዳኑ እግዚአብሔር ጋር የማመሳሰያ መንገድ መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህም እነዚህ ዐረፍተ-ነገሮች ባዶ "እኔ ነኞች" ናቸው ብንል እንኳን፣ በዮሐንስ 8፥58እና 59 በሚገኘው በአንዱ ወቅት ይህንን ሲናገረው፣ የብሉይ ኪዳኑ አምላክ ነኝ በማለቱ ሊወግሩት ድንጋይ አነሱ፡፡ ሌሎቹ "እኔ ነኞች" ከአንድ ነገር ጋር ማለትም "እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ፣" "እኔ ብርሃን ነኝ፣" "እኔ መንገድ እውነትና ሕይወትም ነኝ" የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ኢየሱስ አምላክነቱን ያወጀባቸው ስፍራዎች ናቸው፣ ግን ከሰው ሕይወት ጋር የተዛመደ አምላክ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህን በምናነብበበት ወቅት ሁሉንም አንድ ላይ በማያያዝ እና ዮሐንስ ሊያስተላልፍልን የፈለጋቸው ኢየሱስ የሠራቸው ነገሮች ዘገባ "ይህ ሰው ቀድሞም ነበረ ምክንያቱም አምላክ ነውና" ለማለት መሆኑን ማወቅ ይገባናል፡፡ በዮሐንስ 858 ውስጥ "አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ" ሲል፣ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ነበርሁ ለማለት ሳይሆን፣ ከአብርሃም ጋር የተገናኘ እና ዘላለማዊ አምላክ መሆኑን ለማወጅ ነው፡፡ (ዶ/ር ጆን ማኪንሌይ)**

በዮሐንስ 8፥12-59 ውስጥ ኢየሱስና የአይሁድ መሪዎች በከረረ ግጭት ውስጥ ገብተው ነበር፡፡ ክርክሩ የኢየሱስ ወልድ ነኝ ማለትና የተቃዋሚዎቹ የአብርሃም ልጆች ነን ባይነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በቁጥር 44 ውስጥ፣ እውነተኛ አባታቸው ዲያቢሎስ መሆኑን ኢየሱስ ነገራቸው፡፡ በምላሹም አንተ ከአብርሃም ትበልጣለህን? በማለት ይሞግቱት ነበር፡፡ ኢየሱስም ሙግቱን በዮሐንስ 8፥58 እንዲህ ደመደመው፡፡

### አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ (ዮሐ 8፥58)

ልክ ተፈጥሯዊ እንደሆነው ዓይነት ከአብርሃም እበልጣለሁ እንደሚባል ዓይነት ኢየሱስ "እኔ ነበርሁ" አላለም፡፡ ያለው "እኔ ነኝ" ነው ይህም የአብርሃም ታላቅና ከአብርሃም የምበልጥ ነኝ ለማለት ብቻ ሳይሆን፣ የእስራኤል ዘላለማዊ አምላክ ራሱ ነኝ ማለቱ ነው፡፡

የኢየሱስን መለኮትነት ከተመለከትን፣ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ የሚለውን የዮሐንስን ዐረፍተ-ነገር፣ ኢየሱስ ራሱ ፍፁም ሰው ነበር የሚለውን እውነታ እንመልከት፡፡

## ሰው

ከዳዊት ዘመን ጀምሮ፣ “የእግዚአብሔር ልጅ” የሚለው ቃል በመላው እስራኤል ላይ በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጠውን ሰብዓዊ ንጉሥ ለማመልከት አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡ ይህንንም በመዝሙር 2 ቁጥር 7 እና በ2ኛ ሳሙኤል 7፥14 ውስጥ እናያለን፡፡ ዮሐንስ 7፥42 ክርስቶስ ከዳዊት ዘር እንደሚመጣ አይሁድ ይጠብቁ እንደነበር ያሳየናል፡፡ በዮሐንስ 149 ውስጥ፣ “የእግዚአብሔር ልጅ” የሚለው ቃል “የእስራኤል ንጉሥ” ተምሳሊት ሆኖ አገልግሏል፡፡

በዮሐንስ ወንጌል የሚገኙ በርካታ ምንባቦችም ኢየሱስን ከአይሁድ ንጉሥ ጋር አዛምደውታል፡፡ እነርሱም 12፥13-15፣ 18፥33-40 እና 19፥1-21 ናቸው፡፡ በአጭሩ፣ ዮሐንስ ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ ሲለው፣ በእስራኤል ላይ ለዘላለም የሚገዛ የዳዊት ሰብዓዊ ወገን ነው የማለቱ አንዱ አካል ነው፡፡

የዮሐንስ ወንጌል የእግዚአብሔር ልጅ የሚለውን አፅንዖት ሲሰጠው፣ ኢየሱስ ሙሉ መለኮታዊ እና ሙሉ ሰብዓዊ ንግሥና ያለው ነው ማለቱ ነው፡፡ እግዚአብሔር በፍጥረተ ዓለሙ ላይ እንደሚነግሥ ብሉይ ኪዳን የሰጠው ተስፋ ሁሉ፣ ከዳዊት ዘር የሆነው መሲህ ስለ ሚመሠርተው አገዛዝ ብሉይ ኪዳን የተናገረው ተስፋ ሁሉ፣ የተፈፀመው በኢየሱስ ንግሥና ነው፡፡

አስካሁን፣ በኢየሱስ ማመን፣ የኢየሱስ ማንነት እንደ ክርስቶስና እንደ እግዚአብሔር ልጅ የተሰኙትን መሪ ሃሳቦች ተመልክተናል፡፡ ስለዚህ አሁን በክርስቶስ ያመኑት ስለሚያገኙት የሕይወት በረከት ለመመልከት እንዘጋጃለን፡፡

# ሕይወት

ዮሐንስ በወንጌሉ “ሕይወት” የሚለውን ቃል 36 ጊዜ ያህል ጠቅሶታል፡፡ ሌሎቹ ሦስት ወንጌላት በድምሩ 16 ጊዜ ብቻ ተጠቅመውበታል፡፡ ነገሩ እንዲያው የቁጥር ብዛት የመጥቀስ ጉዳይ ሳይሆን “ሕይወትን” የመስጠቱ ጉዳይ በዚህ ወንጌል ትልቅ ስፍራ አለው፡፡ “ሕይወት” በወንጌል መልዕክት ውስጥ የሚጫወተው ሚናም ሌላው ጉልህ ነገር ነው፡፡ በዮሐንስ 17፥3፣ ኢየሱስ “ሕይወትን” እንዲህ ገልጾታል፡

> ***እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት። (ዮሐንስ 17፥3)***

በእርግጥም፣ ይህኛው እውቀት ስለ እግዚአብሔር ከሚኖረን አዕምሯዊ መረዳት የዘለለ ነው፡፡ ስለ እግዚአብሔር ማስተዋል የሞላበት ግንዛቤንም ያካትታል፡፡ ከዚህ እጅግ የሚልቀው ግን ከእርሱ ጋር ያለው ዝምድና ማለትም በሕይወታችን የእርሱን መገኘትና አብሮነት በግል የመለማመዳችን ነገር ነው፡፡ ይህ ከፈጣሪ ጋር የሚኖረን ህብረት የሰው ዘር የመኖሩ አንዱ ዋና ግብ ነው፡፡ ዮሐንስ 3፥16 እንደሚናገረው፣ ይህ ሕይወት “ዘላለማዊ” ተብሎ ይጠራል፣ ማለትም ማለቂያ የለውም ማለት ነው፡፡ ይህንን ዘላለማዊ ሕይወት ለመቀበል መሞት የግድ አለመሆኑን ዮሐንስ ግልፅ

አድርጎታል፡፡ በመሠረቱ፣ አማኞች የዘላለምን ሕይወት አግኝተዋል፡፡ ኢየሱስ በዮሐንስ 5፥24 እንዲህ ብሏል፡

> *ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም። (ዮሐንስ 5፥24)*

ሕይወት በኢየሱስ ላመኑ የተሰጠ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፡፡

> *ታውቃላችሁ፣ የዘላለም ሕይወት ወደ እኛ በቀላሉ እንደመጣ ሁሉ ቃሎቹም በቀላሉ ተሰብስበው ወደ እኛ ይመጣሉ ምክንያቱም በቅዱሳት መጻሕፍት ደጋግመን እንጋፈጣቸዋለንና ነው፡፡ በክርስቶስ አማካይነት ካገኘናቸው የድነት ስጦታዎች መካከል አንዱ የዘላለም ሕይወት ነው፡፡ ግን ታውቃላችሁ፣ እኛ በዘመን ቅደም ተከተል የምናምን ሰዎች ነን፡፡ የምናስበውም በዚው መንገድ ነው፡፡ በሰከንዶች፣ በደቂቃዎች፣ በሰዓታት፣ በቀናት፣ በወራትና በዓመታት ሚዛን እናስባለን፣ ስለዚህም የዘላለም ሕይወት ማለት አሁን የምናውቀው፣ ረጅም የዘመን ቁጥር የሚሸፍን፣ ያም ማለቂያ የሌለው የዘመን ቀጥር እነደሆነ እናስባለን፡፡ ያ ግን በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊው የዘላለም ሕይወት አስተሳሰብ አይደለም፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የዘላለም ሕይወት የመጀመሪያ ፍቺ በእግዚአብሔር የሚገኝ ሕይወት ማለት ነው፡፡ ያም እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው፡፡ በእኛ ፍጥረቱ በሆንነው የሰው ዘሮችና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ተቃርኖ እኛ ጊዜያዊ መሆናችን ነው፡፡ እኛ ጊዜ ይገድበናል፡፡ እግዚአብሔር ግን በጊዜ አይገደብም፡፡ ክርስቶስ ለእኛ ካስገኘው ስርየት የተነሳ፣ በኢየሱስ የሆኑት ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ሕይወት ይገባሉ፡፡ ስለዚህም፣ የዘላለም ሕይወት ማለት እኛ በክርስቶስ ሕያዋን ሆነን ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም እንኖራለን ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ገፁ ማብቂያ የሌለው ካላንደር ማለት ሳይሆን፣ ዘላለማዊ በሆነው በእግዚአብሔር በራሱ ማንነት ላይ የተመሠረተ፣ የመኖር ጉዳይ ነው፡፡ ግን ታውቃላችሁ፣ ከባለ ሁለት ስንኝ ግጥም ውስጥ ሁለተኛው "ሕይወት" የተሰኘው ቃል በጣም ወሳኝ ነው፡፡ ምክንያቱም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በሕይወትና በሞት መካከል ንጽጽር አለ፡፡ ከፍርድ በኋላ ደግሞ፣ በዘላለም ሕይወትና በሁለተኛው ሞት መካከል ንጽጽር አለ፡፡ ስለዚህ፣ የዘላለም ሕይወት በክርስቶስ፣ ኃጢአታቸው ይቅር የተባለላቸው ሁሉ፣ ከእግዚአብሔርና ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም እንደሚኖሩ የምናረጋግጥበት ነው፡፡ እኛ ለዘላለም በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ እንሆናለን፣ በጊዜ ወደማይገደብ ኑባሬም እንገባለን፣ ዘላለም፣ ማለትም በእግዚአብሔር ክብር እና በመገኘቱ ውስጥ ሆነን በመጽናናትና በደስታ ለዘላለም እያመሰገንነው እንኖራለን፡፡ የዚህ ተቃራኒው ሲያል ነው፣ ያም ሁለተኛው ሞት ተብሏል፡፡ ስለዚህ አሁን ያወራነው የዘላለም ሕይወት የዘላለም ርዝማኔ ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ በሲያል ለዘላለም ከመጣል ይልቅ፣ ከክርስቶስ ጋር የመሆን እና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የማድረግ ባለጠግነት ነው፡፡ (ዶ/ር አር. አልበርት ሞህለር. ትንሹ)*

የዘላለም ሕይወት ከመለኮታዊ ፍርድ ነፃ በመውጣት ማለቂያ ወደሌለው ደስታና ሰላም የመግባት ስጦታ ነው፡፡ የሚገኘውም በልጁ በኢየሱስ በማመን ከእግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ የዮሐንስም

ወንጌል ለዚህ ቢያንስ ሁለት ምክንያቶችን ያቀርባል፡፡ በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ ፈጣሪና የሕይወት ምንጭ ነው፡፡ ይህንንም በዮሐንስ 1፥1-5፣ 5፥26፣11፥25 እና 14፥6 ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ ስለዚህም ኢየሱስ ለፈቀደው ሁሉ ሕይወትን የመስጠት መብት አለው፡፡ እንዲያውም ኢየሱስ ይህንን ነጥብ በዮሐንስ 5፥21 በግልፅ አስቀምጦታል፡፡

የዘላለም ሕይወት የሚገኘው በኢየሱስ ብቻ የመሆኑ ሁለተኛ ምክንያት የሕይወት ቃል ማለትም ሰዎችን ወደሚያድነው አምላካዊ እውቀት የሚመራ የወንጌል መልእክት ያለው ኢየሱስ ብቻ ስለሆነ ነው፡፡ ኢየሱስ ይህንን በዮሐንስ 6፥63 እና 12፥49-50 ውስጥ አብራርቶታል፡፡ ጴጥሮስም በዮሐንስ 6፥68 አረጋግጦታል፡፡

ኢየሱስ "አንድ እርሱ ብቻ"፤ ወይም በዮሐንስ 1፥18 "አንድ ልጁ እርሱ" ተብሏል፡፡ ሰማያዊውን አባት እንደ ኢየሱስ የሚገልጥ ማንም የለም፣ ምክንያቱም እንደ ኢየሱስ ከአብ የወጣ ማንም የለምና፡፡ የኢየሱስ የእግዚአብሔር መገለጥ የመሆን ሃላፊነቱ የተመሠረተው አብን ሊያሳየን እና የዘላለምን ሕይወት ሊሰጠን በመጣው "አንድ ልጁ እርሱ" በሆነው ማንነቱ ላይ ነው፡፡

እናም በዮሐንስ ወንጌል በጠቅላላ፣ ኢየሱስ ለሚያምኑ ሁሉ የዘላለምን ሕይወት የሚሰጥ ነው፡፡ የማያምኑቱ ቃሎቹን አይረዱም፣ ስለዚህ የሚሰጠውን ሕይወት አይቀበሉም፡፡ ያመኑት ግን የዘላለምን ሕይወት አሁኑኑ፣ በሚመጣውም ዘመን የማይቆጠረውን በረከት ይቀበላሉ፡፡

# 5. ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት፣ የዮሐንስን ወንጌል ዳራ ከጸሐፊውና ከተጻፈበት ወቅት አንፃር ተመልክተናል፤ ውቅሩንና ይዘቱንም ዳሰሰናል፤ ማመን፣ የኢየሱስ ማንነት እንደ ክርስቶስና የእግዚአብሔር ልጅ ደግሞም በስሙ የሚገኝ የሕይወት በረከት የተሰኙ ዐቢይ ርዕሶችንም ተመልክተናል፡፡

የእግዚአብሔር የበረከት ተስፋዎች ሁሉ ፍፃሜ ኢየሱስ መሆኑን የዮሐንስ ወንጌል ያሳየናል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ኢየሱስ የሚያድነው የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ የእግዚአብሔርን የከበሩ ተስፋዎች ፈጽሟል ይፈጽማልም፡፡ እነዚህ ተስፋዎችና መዳናችን አስደናቂውን የዘላለም ሕይወት ስጦታ ያካትታሉ፡፡ የዮሐንስን ወንጌል በምናነብበት ወቅት እነዚህን ተስፋዎች አፅንተን ከያዝን፣ ለመረዳትና በሕይወታችን ለማዛመድ ዝግጁ እንሆናለን፡፡ በምንኖርበትም ዘመን ከጠበቅናቸው፣ እግዚአብሔርን ለማክበር እና በልጁ በኢየሱስ በኩል በሰጠን የዘላለም ሕይወት ደስ ለመሰኘት ዝግጁዎች እንሆናለን፡፡